የፍትሕ ሚኒስቴር
MINISTRY OF JUSTICE

ሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀትና መገልገል የሚያስከትለው የህግ ተጠያቂነት የንቃተ-ህግ የስልጠና ሰነድ

በንቃተ ህግ፣ ትምህርት እና ስልጠና ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ



ማውጫ

ርእስ **ገጽ**

መግቢያ.....3

የስልጠና ሰነዱ አላማ.....4

ክፍል አንድ

1.ሀሰተኛ ሰነድና ማስረጃ በጠቅላላው----------5

1.1. የሀሰተኛ ሰነድ ምንነት----------6
1.2. የሰነድ ምንነት----------7
1.3. የሰነድ አይነቶች----------8
1.4. የሀሰት ምንነት----------11
1.5. የማስረጃ ምንነት----------11
1.6. የማስረጃ አይነቶች----------12
1.6.1.የሰው ማስረጃ----------12
1.6.2.የሰነድ ማስረጃ----------12
1.6.3.የባለሞያ ማስረጃ----------13
1.6.4.ገላጭ ማስረጃ----------14
1.7. ሀሰተኛ ማስረጃ----------16
1.8. ሀሰተኛ የሰነድ ማስረጃ----------17

ክፍል ሁለት

2. የሀሰተኛ የሰነድ ማስረጃ የሚያስከትለው የህግ ተጠያቂነት----------21

2.1. የወንጀል ተጠያቂነት በጠቅላላው----------21

2.2. ሀሰተኛ የሰነድ ማስረጃ የሚያስከትለው የወንጀል ተጠያቂነት----------22

2.3. የሀሰተኛ የሰነድ ማስረጃ ማዘጋጀት እና መገልገል በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.የወንጀል ህግ.....23

2.4. የሀሰተኛ የሰነድ ማስረጃ ማዘጋጀት እና መገልገል በልዩ ልዩ አዋጆች.....26

2.5. የፍትሀብሄር ተጠያቂነት በጠቅላላው----------29

2.6. ሀሰተኛ የሰነድ ማስረጃ የሚያስከትለው የፍትሀብሔር ሃላፊነት----------31

2.7. ሀሰተኛ የሰነድ ማስረጃ የሚያስከትለው አስተዳደራዊ ሀላፊነት----------32

ማጠቃለያ----------33

ዋቢ መጻህፍት----------34

መግቢያ

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፍትህ ሚኒስቴር በፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 943/2008 አንቀጽ 6(9) እና የፌደራል አስፈጻሚ አካላት ስልጣን እና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 40 መሰረት ከተጣለበት ሀላፊነት መካከል የተቋሙን ባለሞያዎች እና አመራሮች እንዲሁም ለሌሎች የመንግስት አከላት ስልጠና በመስጠት የባለሞያውን እና አመራሩን የማስፈጸም አቅም ማሰደግ አንዱ ነው። በተጨማሪም የማህበረሰቡን ንቃተ ህግ በማሳደግ ወንጀልን የሚጸየፍ ለሰላም መስፍን የሚተጋ ለህግ እና ፍትህ መከበር የበኩሉን አስተዋጸ የሚያደርግ ማህበረሰብ መገንባት ውስጥ ፍትህ ሚኒስቴር ግንባር ቀደም ሚና አለው።

የስልጠና እና ንቃተ ህግ ስራን አቀናጅቶ እንዲሰራ በመንግስት ህግ እና ፍትህ አገልግሎት ዘርፍ ስር የንቃተ ህግ፤ ትምህርትና ስልጠና ዳይሬክቶሬት ተዋቅሮ የስልጠና እና የንቃት ህግ ስራዎችንም እያከናወነ ይገኛል። ከዚህ ተልእኮ መሳካት አንጻር በየበጀት አመቱ የሚሰሩ የንቃተ ህግ ስራዎችም ሆኑ የአቅም መገንቢያ ስልጠናዎች የሚሰጡት የህብረተሰቡን ፍላጎት መሰረት በማድረግ ነው። ስልጠናዎችም የሚሰጡት በመስሪያ ቤቱ እና ሌሎች በፍትህ ተቋማት ከህግ ማስፈጸም አንጻር የሚገጥሟቸውን ተግባራዊ ችግሮች መሰረት በማድረግ የክህሎትን ለማዳበር በማለም መሆኑ ይታወቃል። ለዚህ ስራ መቃናት የንቃተ ህግ ትምህርት ርእሶችን እና የስልጠና ርእሶችን በመለየት በየአመቱ የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት በማድረግ ወደስራ የሚገባ ሲሆን በያዝነው በጀት አመትም ይሄው የዳሰሳ ጥናት ተካሂዶ ወደ ትግበራ ተገብቷል። በዚህ ዳሰሳ ጥናት መሰረት ለሕብረተሰቡ የንቃተ ህግ ትምህርት እንዲሰጥባቸው ከተለዩ የህግ ጉዳዮች አንዱ ሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀት እና መገልገል ወንጀል ነው።። ለባለሞያዎች ስልጠና ቢሰጥባቸው ተብለው ከተለዩ የህግ አርስተ ጉዳዮች መካከልም ይሄው ሀሰተኛ ሰነድ መፍጠር እና መገልገል ወንጀል ይገኝበታል።

ከፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ባሻገር በተግባር የሚታዩ ችግሮችን ብናይ ምንም እንኳን ይህ ወንጀል አልፎ አልፎ የሚፈጸም ወንጀል የነበረ ቢሆንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን አድማሱን እያሰፋ ያለ የዜጎችን መብት እና መንግስትንም እየጎዳ ያለ ወንጀል መሆኑ አያጠያይቅም። ወንጀሉን አስከፊ የሚያደርገው በባለሞያዎች ታግዞ በቀላሉ ሊደረስበት በማይቻለበት መንገድ የሚፈጸም ወንጀል በመሆኑ ነው። በቅርብ ጊዜያት የሚወጡ መረጃዎችን ብናይ እንኳን ከመደበኛው የወንጀሉ ባህሪ ወጣ ባለ መልኩ የህግ ባለሞዎች ጭምር የዚህ ወንጀል ፈጻሚ

ሆነው የተከሰሱበት ሂደት እንዳለ ይታወቃል። ከዚህም የምንረዳው በሰነዶች ላይ የሚፈጸመው ወንጅል እጅግ እየሰፋ በውጤቱም የሀገርን እና ዜጎችን የኢኮኖሚ ጥቅም እጅግ እየጎዳ ያለ ወንጀል መሆኑን ነው።

ሀሰተኛ ሰነድ መፍጠር እና መገልገል ወንጀልን ለመከላከል በኢ.ፌ.ድ.ሪ.የወንጀል ህግ እና በወንጀል ፍትህ ፖሊሲው መሰረት ቅድሚያ የሚሰጠው ወንጀሉ እንዳይፈጸም መከላከል ነው።። በወንጀል መከላከል ውስጥ ደግሞ የህብረተሰቡ ንቃተ ህግ እጅግ ከፍተኛ ቦታ አለው። መብትና ግዴታውን በውል ለይቶ የሚያውቅ ወንጀልን የሚጸየፍ ማህበርሰብ መፍጠር ለዚህ ሁነኛ መንገድ ነው።። እንዲህ ያለ ማህበረሰብ ሀሰተኛ ሰነድ ለሚያዘጋጁም ሆነ ይሄንኑ ሰነድ የሚገለገሉ ሰዎች መሸሸጊያ ከመሆን እራሱን ያቅባል።

በዚህም መሰረት ይህ የስልጠና ሰነድ ማህበረሰቡን ሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀት እና መገልገል የሚያስከትለውን የህግ ተጠያቂነት በመዳሰስ ማህበረሰቡን በዚሁ ጉዳይ ዙሪያ ለማሰልጠን ታስቦ የተዘጋጀ ሰነድ ነው።

የስልጠና ሰነዱ በዋናነት በሁለት ክፍል የተዋቀረ ነው። በክፍል አንድ ስለ ሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀት እና መገልገል የሚስከትለው የህግ ተጠያቂነት ጠቅላላ ግንዛቤን ለመፍጠር በማሰብ ስለ ሀሰተኛ ሰነድ ምንነት የምንዳስስ ይሆናል። በዚህም የሀሰተኛ ሰነድን ምንነት፣ የማስረጃ አይነቶችን፣የሀሰተኛ ማስረጃ ምንነት እና የመሳሰሉት ጉዳዮች የሚዳሰሱ ይሆናል። በክፍል ሁለት ሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀትና መገልገል እና የሚያስከትለው የወንጀል ተጠያቂነት የምንዳስስ ይሆናል።

የስልጠና ሰነዱ አላማ

ሀሰተና ሰነድ መፍጠር እና መገልገል ወንጀል በተቻለ አቅም እንዳይፈጸም መከላከል ከተፈጸመም አጥፊዎችን በህግ ለመቅጣት የንቃተ ህግ እና ስልጠና ስራዎች የማይተካ ሚና አላቸው።

ማህበረሰቡም በእነዚህ ወንጀሎች ላይ ግንዛቤ ይዞ በሰነድ ከሚፈጠሩ ወንጀሎች እራሱንም ሆነ ሌሎችን እንዲሁም አገሩን እንዲጠብቅ አስፈላጊ ሲሆን ከፍትህ አካላት ጋር ተባበሮ አጥፊዎችን እንዲጠየቁ በማድረግ ውስጥ ማለትም ወንጀሉን በመጠቆም ፣ምስክር በመሆን የራሱን ሀላፊነት እንዲወጣ ማድረግ ያስፈልጋል። ይህ አጭር የስልጠና ሰነድ የተዘጋጀው ይሄንኑ ዋና አለማ ለማሳካት በማሰብ ነው።

በዚህም መሰረት የህ የስልጠና ሰነድ የሚከተሉት ዝር ዝር አላማዎች አሉት፡-

- የማህበረሰቡን ንቃተ ህግ በማሳደግ ሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀት እና መገልገል ወንጀልን መከላከል፤
- ሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀት እና መገልገል ወንጀልን ተፈጽሞ ሲገኝ ማህበረሰቡ ለፍትህ አካላት ተገቢውን ድጋፍ አድርጎ ወንጀለኞች እንዲጠየቁ የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ ማስቻል፤ እና
- ሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀት እና መገልገል ወንጀልን የሚከላከሉ ባለድርሻ አካላት በጉዳዩ ላይ የጋራ ግንዛቤ ኖሯቸው በትብብር እና በቅንጅት እንዲሰሩ ማድረግ፤

  ናቸው።

ክፍል አንድ

1. ሀሰተኛ ሰነድና ማስረጃ በጠቅላላው

በፍትህ ስርአት ወስጥ ማስረጃ የጀርባ አጥንት ነው። በዚህም ፍትህብሄራዊ ክርክር ውስጥ አከራካሪ የሆኑ ፍሬ ነገሮችን እውነትነት ለማረጋገጥ ወይም በወንጀል ምርምራ እና ክርክር ውስጥ የተባለው ወንጀል መፈጸም አለመፈጸሙን ለማረጋገጥ የሚቻለው ማስረጃ ሲኖር ብቻ ነው። በፍትህ ስርአት ውስጥ ማስረጃ የማይተካ ሚና አለው ሲባልም ይሄንኑ እውነት ታሳቢ በማድረግ ነው። በስፋት ስራ ላይ የሚውሉ ማስረጃ አይነቶችን ስናይ የሰው ምስክርነት፣የሰነድ ማስረጃዎች፣ የባለሞያ ማስረጃዎች እና ገላጭ ማስረጃዎች ይገኙበታል።

በዚህ የስልጠና ጽሁፍ በዋናነት ትኩረት የምናደርግበት በሰነድ ማስረጃ ላይ የሚፈጸም የሀሰት ተግባር እና በሀሰት የተዘጋጀውን የሰነድ ማስረጃ መጠቀም የሚያስከትለውን ጉዳት እና የህግ ተጠያቂነት ነው።

በሰነድ ማስረጃ ላይ የሚፈጸሙ ጥፋቶችን ከማየታችን በፊት ሰልጣኞች በጉዳየ ላይ ግልጽ አረዳድ እንዲኖራቸው በማሰብ በቅድሚያ በዚህ ክፍል የሀሰተኛ ሰነድ ምንነት እና በጥቅሉ የሀሰት ማስረጃ ምን እንደሆነ አንዳንድ ነጥቦችን በማንሳት የምናይ ይሆናል።

1.1. የሀሰተኛ ሰነድ ምንነት

ስለ ሀሰተኛ ሰነድ ምንነት ከማንሳታችን በፊት የቃሉን አፈጣጠር ማንሳቱ ተገቢ ነው። በዚሁ መሰረት ሀሰተኛ ሰነድ ከሚለው ንባብ መረዳት እንደሚቻለው ሀሰተኛ ሰነድ የሚለው ሀረግ ከሁት አማርኛ ቃላት የተመሰረተ ሲሆን እነሱም ሀሰት እና ሰነድ የሚሉ ናቸው። በዚህ ጽሁፍ ውስጥ በስፋት የተዳሰሱ ጉዳዮች በመሆናቸው የነዚህኑ ቃላት ትርጉም አንድ በአንድ እንደሚከተለው እናያለን። በቅድሚያም የሰነድን ምንነት ከዳሰስን በኋላ ስለሀሰት የምናይ ይሆናል።

1.2. የሰነድ ምንነት

ሰነድ የሚለው ቃል በተለያዩ መዝገበ ቃላት ትርጉም የተሰጠው ቃል ሲሆን በፍትህ ስርአት ውስጥም ሆነ በሌሎች መህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ውስጠ እለት ተእለት የምንጠቀምበት ቃል ነው። ትርጉሙን በተመለከተ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነጽሁፍ ጥናት መዝገበ ቃላት መሰረት ሰነድ ማለት ስለ አንድ ጉዳይ መረጃዎችን የያዘ የጽሁፍ መዝገብ ወይም ማስረጃ ማለት ነው ሲል ገልጸት ይገኛል።[1]

በመደበኛ የኢንግሊዘኛ መዝገበ ቃላት ትርጉም መሰረት ሰነድ ማለት document በሚለው ቃል የታወቅ ሲሆን አሱም any written item, as a book, article, or letter, especially of a factual or informative nature.[2] ሲሆን ትርጉሙም ማንኛውም የተጻፈ ነገር ሲሆን መጻህፍትን፣ደብዳቤዎችን፣እና ሌሎች መሰል ነገሮችን የሚያካትት ሲሆን በተፈጥሮው መረጃ ሰጪ የሆነ ነገር ነው።

በሌላ በኩል ታዋቂው ብላክስ ለው መዝገበ ቃላት ሰነድን በእንግሊዘኛ አቻ ቃሉ document ለሚለው ቃል የሰጠውን ትርጉም ስናይ …..an instrument on which is recorded, by means of letters, figures, or marks, matter which may be evidentially used. In this sense the term "document" applies to writings; to words printed, lithographed, or photographed; to seals, plates, or stones on which inscriptions are cut or engraved; to photographs and pictures: to mans or plans. The inscription may be of stone or gems, or on wood, as well as on paper or parchment.[3] በሚል አስቀምጦት እናገኛለን። ከዝህ ትርጉም የምንረዳው ብለክስ ለው የህግ መዝገበ ቃላት ለሰነድ ምንነት የሰጠው ትርጉም ከመደበኛዎቹ መዝገበ ቃላት ሰፋ ያለ መሆኑን ነው። በዚሁም መሰረት ሰነድ በማስረጃነት ሊያገለግሉ የሚችሉ መረጃዎች በጽሁፍ፣ በስእል፣ በማሳያ ነገሮች የተመዘገበበት ወይም የተቀረጹበት ማናቸውም ነገር ሲሆን

---

[1] አማርኛ መዝገበ ቃላት፣አትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምርምር ማእከል፣አዲስ አበባ የኑቨርሲቲ፣የካቲት 1993፣ገጽ 119

[2] < https://www.collinsdictionary.com/dictionary/english/document>

[3] HENRY CAMPBELL BLACK, M. A. BLACK'S LAW DICTIONARY 4rth edition, WEST PUBLISHING CO. 1968

, https://heimatundrecht.de/sites/default/files/dokumente/Black%27sLaw4th.pdf ,

እነዚህ መረጃ የተቀረጸባቸው ወይም የተመዘገቡባቸው ነገሮች፣ ወረቀቶች፣ ድንጋዮች እንጨቶች፣ ጨርቆች እና ወዘተ ሊሆኑ ይችላሉ።

መዝገበ ቃላቱ ለሰነድ የሰጡትን ትርጉም በዚህ ልኩ ካነሳን በህግ ደረጃ ለጉዳዩ የተሰጡ ትርጉሞችን ስናይ በሰነዶች ማረጋገጫ እና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 922/2008 አንቀጽ 2 ንኡስ አንቀጽ 1 ላይ እንደተደነገገው "ሰነድ" ማለት ማናቸውም ውል፣ ኑዛዜ፣ የውክልና ሥልጣን መስጫና መሳሪያ ሰነድ፣ ከአንድ ቋንቋ ወደ ሌላ ቋንቋ ጽሁፎችን ለመተርጎም ፈቃድ በተሰጠው ሰው የተተረጎመ ጽሁፍ፣ የሰነድ ቅጂ ወይም ግልባጭ፣ የወሳኝ ኩነት ሰነድ፣ የትምህርትና የሙያ ፈቃድ ማስረጃ፣ የማህበራት መመስረቻ ጽሁፍ እና/ወይም መተዳደሪያ ደንብ፣ ቃለ ጉባዔ ወይም ማናቸውም በዚህ አዋጅ መሠረት እንዲረጋገጥና እንዲመዘገብ የቀረበ ጽሁፍ ነው ሲል አስቀምጦታል። ከዚህ ድንጋጌ የምንረዳው ሰነድ በባህሪው መብትን የሚያቋቁሙ ወይም ግዴታን የሚጥሉ በአይነታቸው እጅግ ብዙ የሆኑ ሰነዶችን የሚያካትት መሆኑን ነው። ከመዝገበ ቃላቱ ትርጉም አንጻር ሲታይ በዚህ አዋጅ በሰነድነት የተገለጸው በጽሁፍ መልክ የተዘጋጀና በወረቀት ላይ ያረፈ ሰነድ ብቻ ይመስላል። በመዝገበ ቃላቱ ግን ይህ ማስረጃ ወይም መረጃ የግዴታ በወረቀት ላይ ብቻ የተገለጸ መሆን አይጠበቅበትም።

1.3. የሰነድ አይነቶች

ሰነዶች በዋናነት በሶስት ተከፍለው ሊታዩ ይችላሉ። እነሱም የመንግሰት፣ የህዝባዊ ድርጅቶች ወይም የግል ሊሆኑ የችላሉ። የመንግስት ሰነዶች የሚባሉት መንግስት ህዝባዊ አገልግሎት ለመስጠት እንዲያስችለው ለተገልጋይ ግለሰቦች፣ ቡድኖች እና ድርጅቶች የሚሰጣቸው የመለያ ወይም አስቻይ ወይም ፈቃጅ ሰነዶች እነዲሁም ተቋማቱ ስራቸውን በማከናወን የሚያመነጯቸው ወይም ወጪ የደርጓቸው ሰነዶችን ይጨምራል። እነዚህ ሰነዶች የሚይዙት መረጃ ባለሰነዱ ከመንግስት ጋር ያለውን ግንኙነት የሚያሳዩ ናቸው። የመንግስት ሰነድ የሚሰጠው በመንግስት አካላት ሲሆን እነሱም በየደረጃው ያሉ አስፈጻሚ አካላት ለምሳሌ የወሳኝ ኩነት እና ኢሚግሬሽን ኤጀንሲ፣የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር፣ ፍርድ ቤቶች፣ፍትህ ሚኒስቴር፣ የሰነዶች ማረጋገጫ እና ምዝገባ ኤጀንሲ፣ የጤና ሚኒስቴር፣ እና ሌሎች የመንግስት አካላት የሚያመነጯቸው ወይም የሚሰጧቸው የሠነድ ማስረጃዎች አሉ። ለምሳሌም፡-

- ፓስፖርት እና ቪዛ ወይም ለውጭ አገር ዜጎች የመኖሪያ ፈቃድ

- የገንዘብ ኖቶች
- ቴምበሮች
- መታወቂያ
- ንግድ ምዝገባ እና ፈቃድ
- የፈቃድ እና ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬቶች
- የትምህርት ማስረጃዎች
- የፍርድ ቤት ውሳኔዎች
- የእውቅና እና ማበረታቻ ሰርተፊኬቶች
- እቅዶች፤ሪፖርቶች
- የመንግስታዊ ተቋም ውሳኔዎች
- ኦፊሴላዊ ወጪ ደብዳቤች እና

የመሳሰሉት ይገኙበታል።

ሌላው የህዝባዊ ድርጅቶች ሰነዶች ሲሆን ህዝባዊ ድርጅቶች ሲባል በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 2 ንኡስ አንቀጽ 4 መሰረት ከህዝብ የተሰበሰበ ገንዘብ ፣ ወይም ለህዝብ አገልግሎት የተሰበሰበ ገንዘብን የሚያስተዳድሩ አካላትን እና አግባብነት ያለው ኩባንያን ይጨምራል። እነዚህም አክስዮን ማህበራት፣ ህብረት ስራ ማህበራት እና የመሳሰሉት ከህዝብ የተሰበሰበ ገንዘብን የሚያስተዳድሩ የግል ድርጅቶችን ያካትታል። ሌላው የመንግስት የልማት ድርጅትች ሰነድንም የሚያካትት ነው። የመንግስት የልማት ድርጅቶች የሚባሉት በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1983 አንቀጽ 2 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት መንግስት ለትርፍ የሚያቋቁማቸውና በማምረት፣ በማከፋፈል ፣አገልግሎት በመስጠት እና መሰል የኢኮኖሚ ዋጋ ያላቸውን ስራዎች የሚሰሩ ድርጅቶች ሲሆኑ ለምሳሌ እንደ ንግድ ባንክ፣ ጥረት፣ ስኳር ኮርፖሬሽን፣ ኢትዮቴሌኮም፣ መብራት ሀይል እና የመሳሰሉትን ያካትታል። በተጨማሪም በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 2 ንኡስ አንቀጽ 3 መሰረት የመንግስት የልማት ድርጅት ማለት የመንግስት የባለቤትነት ድርሻ በሙሉ ወይም በከፊል ያለበት የፌደራል ወይም የክልል መንግስት የልማት ድርጅቶች ወይም አክሲዮን ማህበራትን የያዘ ነው።

እነዚህ ህዝባዊ ድርጅቶች እና የመንግስት የልማት ድርጅቶች የሚሰጧቸው የተለያየ ሰነዶች ያሉ ሲሆን ለምሳሌም፡-

- የክፍያ ሰነዶች
- የአባልነት መታወቂ ሰነዶች
- የአክሲዮን ሰነዶች(securities)
- የመመስረቻ እና መተዳደሪ ደንብ ሰነዶች
- ቃለ ጉባኤ የተያዘባቸው ሰነዶች
- የሂሳብ ደብተሮች
- የእዳ እና ብድር መግለጫ ሰነዶች (Bond and Debenture)
- የክስረት ሀብት የተጣራባቸው ሰነዶች (bankruptcy liquidation documents) እና የመሳሰሉትን ሰነዶች የጨምራል።

የግል ሰነዶችን ስናይ እላይ ካየናቸው የመንግስት፣ የህዝባዊ ድርጅት ወይም መንግስታዊ የልማት ድርጅት ከሚመነጩ ወይም ከሚሰጡ ሰነዶች ውጪ ያሉ ሰነዶች የግል ሰነዶች ሊባሉ ይችላሉ። እነዚህ ሰነዶች ማህበረሰቡ እርስ በርስ ላለው ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ግንኙነት ሲከውን ግንኙነቱ ህጋዊ መሰረት እንዲኖረው ለማድረግ በወረቀት በማስፈር በሰፈሩ ጉዳዮች ላይ የተመሰረቱ ሰነዶች ናቸው። ለምሳሌም፡-

- ውሎች
- ኑዛዜዎች
- ቃለ-መሃላዎች
- ቃለ-ጉባኤዎች እና

የመሳሰሉትን ያካትታል።

1.4.የሀሰት ምንነት

ሀሰት የሚለው ቃል በእለት ተእለት ተግባቦት ስርአታቸን ከምንጠቀምባቸው የአማርኛ ቃላት አንዱ ነው። በኪዳነወልድ ክፍሌ አማርኛ መዝገበ ቃላት መሰረት ሀሰት የሚለው ቃል ትርጉሙን ስናይ ሀሰተ ከሚለው ስርወ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጓሜውም ሳተ፣ አሳሳተ፣ለወጠ፣ቀጠፈ፣ ወዘተ እንደማለት ነው። በማህበረሰባችን ውስጥ ሀሰት እጅግ ጥዩፍ ከሆኑ ተግባሮች አንዱ ነው። ኢትዮጵያ በእለት ተእለት ግንኙነት ውስጥ ስለእውነት

በሚማማል እና ሃሰት ከባህሉ፣ሀይማኖቱ እና ሁለንተናዊ እሴቱ ተቃራኒ እንደሆነ የሚያምን ማህበረሰብ ያላት አገር ናት ።

በማህበረሰቡ ውስጥ አንድ ጉዳይ እውነት ወይም ሀሰት መሆኑ እጅግ ከፍተኛ አንድምታ አለው። በአንድ ጉዳይ ላይ አለመግባባት የሚኖረው አንዱ ወገን ስለጉዳዩ የተነገረው ወይም የተገለጸው ነገር መኖሩ ወይም እውነት መሆኑን የሚሞግት ሲሆን ሌላው ወገን በበኩሉ በተመሳሳይ ሁኔታ የተባለው ነገር አለመኖሩን ወይም በገሃድ የሚታይ እውነትነት የሌለው መሆኑን በማንሳት ሲከራከር ነው።

የፍትህ ተቋማት በተለይም የዳኝነት አካሉ በእንደዚህ ያሉ በአንድ ፍሬ ነገር እውነትነት ወይም ሀሰትነት አልያም መኖር አለመኖር ላይ ሊጣሩ የሚገባቸውን ፍሬ ነገሮች በጭብጥነት በመያዝ የእነዚህኑ አከራካሪ ፍሬ ነገሮች የሚያረጋግጡ ማስረጃዎችን በመስማት በይበልጥ የተረጋገጠውን ሀሳብ በመደገፍ የፍሬ ነገሩን እውነትንት ወይም ሀሰትንት በመበየን ውሳኔ ይሰጣሉ። በወንጀል ምርመራ ሂደትም ፖሊስ እና አቃቤ ህግ ተፈመ ከተባለው ወንጀል ጋር በተያያዘ ያሉ አውነታዎችን ለማጥራት የተለያዩ ማስረጃዎችን በመሰብሰብ እና በመስማት አውነታው ላይ ለመድረስ ይጥራሉ። የውሳኔ ሀሳብ ላይ ለመድረስ ረጅም የማስረጃ መስማት እና ማጣራት ሂደትን ያልፋል። እዚህ ላይ ሊሰመርበት የሚገባው እውነት እና ፍትህ ያላቸውን ግንኙነት ነው። እውነት ሁሌም ቢሆን ፍትሀዊ ስትሆን ፍትህ ግን ሁሌም እውነትን በውስጡ የግድ ላይዝ ይችላል። ፍትህ የማስረጃ ምዘና ውጤት ሲሆን የተሻለ ማስረጃ ያለው ፍሬ ነገር ፍትሃዊ ነው ተብሎ ይበየናል። ነገር ግን የግድ እውነት(reality) ነው ማለት አይደለም። ከሱ በተቃራኒ ያለው የክርክር ሀሳብ ያስነሳው ጉዳይ በተሻለ ማስረጃ ስላልተደገፈ ሀሰት ነው ማለትም አይደለም። ከላይ ባየነው አግባብ እውነት ያልሆነ ነገር ሀሰት ይሆናል ማለት ነው (by elimination theory) ። የሀሰተኛ ሰነድን ምንነት ለመግለጽ ስለ ሀሰትነት ይህን ያክል ካልን ቀጥለን ስለ ሰነድ ምንነት የምናይ ይሆናል።

1.5.የማስረጃ ምንነት

በዳኝነት አሰጣጥ ሂደት የአንድን ፍሬ-ነገር መኖር ወይም አለመኖር ማረጋገጥ የሚቻለው ማስረጃ በማቅረብ ነው። ማስረጃውም የተባለውን ነገር እውነትነት ወይም ሀሰትነት ወይም መኖር አለመኖር የሚያሳይ በስሜት ህዋሳችን አይተን፣ አሽትተን፣ ዳሰን ወይም ሰምተን የምንረዳው እና የምንለየው ነገር ነው። በሌላ መልኩ ደግሞ ማስረጃ ማቅረብ የማያስፈልጋቸው

ፍሬ ነገሮች ያሉ ሲሆን እነሱም አከራካሪ ባለመሆናቸው መኖር አለመኖራቸው ፍርድ ቤት ግምት የሚወሰድባቸው ነገሮች ናቸው።

1.6.የማስረጃ አይነቶች

የማስረጃ አይነቶችን ስናይ ማስረጃዎች በተለያየ መልኩ ሊከፈሉ የሚችሉ ሲሆን ለዚህም እን ደመስፈርት የሚያገለግሉት ማስረጃው ያረፈበት ወይም የተቀረጸበት ነገር ወይም እቃ፣ ማስረጃ ለአከራካሪው ርእሰ ጉዳይ ጋር ያለው ግንኙነት ወይም ቅርበት፣ ማስረጃው በማንኛውም ሰው ሊቀርብ የሚችል ወይም በባለሞያዎች ሊቀርብ የሚችል መሆኑ እና ወዘተ በሚሉ መስፈርቶች የማስረጃ አከፋፈልን ማየት እንችላለን።[4]

ባለሞያዎች እነዚህኑ መስፈርት በመጠቀም ማስረጃን በተለያየ መደብ የሚከፍሉ ሲሆን ጥንታዊ የማስረጃ አረዳድ (classical understanding of evidence) እና አሁናዊ የማስረጃ አይነቶች አረዳድ ብለን በሁለት ጎራ እናያቸዋለን። በዚሁ መሰረት መጀመሪያው ጥንታዊው የማስረጃ አይነቶች አረዳድ በዋናነት ማስረጃው የሚቀርብበትን መንገድ መሰረት በማድረግ በ 4 ዋና ዋና ክፍሎች ይመድባቸዋል። እነሱም የሰው ማስረጃ፣የሰነድ ማስረጃ፣ የባለሞያ ማስረጃ፣ ቀጥተኛ ማስረጃ ወይም ኤግዚቢት ናቸው። በቀጣዩም እነዚህኑ የማስረጃ አይነቶች አጠር አጠር አድርገን የምናያቸው ይሆናል።

1.6.1 የሰው ማስረጃ ወይም ምስክር

ሰዎች በአካል ፍርድ ቤት ቀርበው ያዩትን፣ የሰሙትን፣ የዳሰሱትን፣ የቀመሱትን፣ በአጠቃላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ያወቁትን ነገር መረጃ የሚሰጡበት መንገድ ሲሆን ፍሬ ነገሩን የሚገልፁት በንግግር ወይም በምልክት በሚችሉት ቋንቋ በአስተርጓሚ ሊታገዝ ይችላል። ይህም የምስክርነት ቃል ይባላል። የሰው ማስረጃ ቀጥተኛ ምስክር፣ የአከባቢ ምስክርና የባለሞያ ምስክር በመባል ይታወቃሉ (ይቀርባሉ)።

1.6.2. የሰነድ ማስረጃ

[4] Classification of evidence, Amicus Curea&Co, Nov 6, 2013, http://amicuscuriaeco.weebly.com/discussions/classification-of-evidence ,acessed on 20 january,2023.

ይህ የማስረጃ ዓይነት በላዩ ላይ የተፃፈበት፣ የተሳለበት፣ ወይም ማናቸውም ዓይነት ምልክት የተደረገበት ወይም ድምፅ የተቀዳበት ሆኖ ይዘቱም ለአስረጅነት የሚቀርበው የተፃፈዉ ጽሁፍ ፣የተሳለዉ ስዕል ወይም የተደረገው ምልክት ወይም የተቀዳዉ ወይም የተቀረፀዉ ድምፅ (ምስል) ወይም ማናቸውም ነገር ነዉ። ኮርኔል ለው ስኩል የተባለ ተቋም የሰነድ ማስረጃን ምንነት ሲተረጉም `...any document introduced in trial that is on paper .... The term 'documentary evidence' includes but is not limited to writings, documents, blueprints, drawings, photographs, computer printouts, microfilms, X-rays, files, diagrams, ledgers, books, tapes, audio and video recordings, and papers of any type or description.'[5] በማለት አስቀምጦት እናገኛለን። ከዚህ ትርጉም መረዳት እንደሚቻለው የሰነድ ማስረጃ በተለምዶው ባለው አረዳድ በጽሁፍ ብቻ የቀረበ ማስረጃ መሆኑን ሳይሆን ሰፋ ባለ መልኩ ፎቶግራፎቹን፣ ቪዲዮዎችን፣ ፊልሞችን፣ ዲዛይኖችን ወዘተ. የሚያካትት መሆኑ ነው።

ስለዚህ ለሰነድ ማስረጃነት ዋናው ነገር ማስረጃ የሆነው ፍሬ ነገር (የተፃፈው ቃል የተቀረፀው ምልክት፣ የተሳለዉ ስዕል፣የተቀፀዉ ድምፅ ወይም ምስል) በወረቀቱ፣ በካሴቱ በዕቃዉ፣... ወዘተ ሰፍሮ መገኘቱ ነው።

1.6.3. የባለሞያ ማስረጃ

የባለሞ ማስረጃ አንድ በፍርድ ሂደት አከራካሪ ለሆነ ፍሬ ነገር ምርመራ ጉዳዩን እየመረመረ ላለው መርማሪ ወይም ፍርድ ቤት እውነታው ላይ እንዲደርስበ ለማስቻል በማሰብ በፍሬ ነገሮቹ ከተገለጹት ሃሳቦች ጋር ግንኙነት ባላቸው እና በጉዳዩ ላይ ባለሙያ የሆኑ ሰዎች የሚሰጡት ሞያዊ አስተያየት፣ትንተና ወይም ሞያዊ ምስክርነት ነው። ይሄን ጉዳይ ባለሞያዎች ሲገልጹት "the ever-widening range of scientific and technical knowledge provides the courts of law with new or improved means for the investigation of truth.[6] በማለት ያስቀምጡታል። በዚህ ዙሪያ ባለሞያዎች የሚሰጡት

[5]Cornel Law School,Documentery evidence, LII Legal Information Institute,https://www.law.cornell.edu/wex/documentary_evidence accessed on 28 December,2022

[6] HA Hammelmann,'Expert evidence'Wiley online library,1947, https://onlinelibrary.wiley.com/doi/pdf/10.1111/j.1468-2230.1947.tb00035.x acessed on 02 january,2023

አስተያየት በሞያው የታወቁና በአማካይ አብዛኛውን ባለሙያ በሚያሳምኑ መርሆችን በመከተል አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ይጠበቃል። በአገራች የፍትህ ስርአትም በተለያዩ ጉዳዮች ባለሞያዎች ቀርበው አስተያየታቸውን በመስጠት የፍትህ አካላት ለሚሰጡት ውሳኔ እገዛ ያደርጋሉ። ለምሳሌም የሂሳብ ባለሞያዎች፣የመንገድ ትራፊክ ባለሞያዎች፣ ሰነድ አረጋጋጭ ባለሞያዎች፣ የህክምና ባለሞያዎች፣ የግዢ ባለሞያዎች ወዘተ ይጠቃሳሉ።

1.6.4. ገላጭ ማስረጃዎች

ይህ የማስረጃ ዓይነት ፍርድ ቤት እንዲያየውና ግንዘቤ እንዲወስድበት የሚቀርብ ነገር ነው። ለምሳሌ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ንብረት ወይም ወንጀል ለመፈፀም አገልግሎት ላይ የዋለ መሣሪያ በማስረጃነት ሲቀርብ ገላጭ ማስረጃ ይባላል። አገልግሎቱም ፍርድ ቤቱ ተመልክቶ ግንዛቤ እንዲወስድ ማስቻል ነው።

እነዚህ የማስረጃ አይነቶች የፍትህ አካላት በእለት ተእለት ስራቸው አከራካሪ ፍሬ ነገሮችን ለማጣራት እና ለመወሰን የሚጠቀሙባቸው ናቸው።

ሌላው እና በአሁናዊ የማስረጃ አይነቶች አረዳድን ስናይ የተለያዩ መስፈርቶችን መሰረት በማድረግ ማስረጃን በ20 አይነት ከፋፈሎ የሚያሳየን ነው።[7]

እነሱም፡-

1. ቀጥተኛ ማስረጃ(direct evidence) ከጉዳዩ ወይም ከፍሬ ነገሩ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት እና አግባብት ያለው ማስረጃ አይነት ነው።)
2. አካባቢዊ ማስረጃ (circumstantial evidence) ከጉዳዩ ወይም ከፍሬ ነገሩ ጋር ቀጥተኛ ያልሆነ ግንኙነት ያለው ነገር በአካባያዊ ሁኔታ ጉዳዩን በማስረዳት የሚያግዝ የማስረጃ አይነት ነው)
3. ግዙፋዊ ማስረጃ (physical evidence) አንድን ፍሬ ነገር የሚያስረዳ ማንኛውም ቁስ ወይም ማቴሪያል ነው)

---

[7] Jess scherman, *'20 Types of Evidence You May Encounter as a Paralegal'*,RassMUssen University,2019, https://www.rasmussen.edu/degrees/justice-studies/blog/types-of-evidence/
Accessed on 12 december,2022

4. **የግለሰብ ግዚፋዊ ማስረጃ** (individual physical evidence) (**ግለሰብን የተመለከተ ፍሬ ነገር የሚያመለክቱ የግል ቁሶች ወይም ንብረቶች …ለምሳሌ** DNA፣ **አሻራ ወዘተ**)
5. **የቡድን ግዙፋዊ ማስረጃ**(class physical evidence) **ቡድንን የሚመለከት ፍሬ ነገር የሚያሳይ ማስረጃ ነው። ለምሳሌ የደም አይነት፣ የጦር መሳሪያ ሞዴል ወይም አይነት፣ የጫማና አልባሳት ሞዴል፣ ቁጥር እና አይነት ወዘተ**)
6. **ፎረንሲክ/አሻራ ማስረጃ** (**በሳይንሳዊ መንገድ የተረጋገጠ ማስረጃ**)
7. **የንክኪ ማስረጃ**/Trace evidence) (**ወንጀል የተፈጸመባቸው ማቴሪያሎችን ለመለየት በመካከላቸው ንክኪ መኖሩን የሚያሳይ ማስረጃ ሲሆን ለምሳሌ የጦር መሳሪያ ባሩድ፣ጸጉር፣አፈር ፣ የጎማ ምልክት፣ የኮቴ ምልክት፣ ወዘተ..ለዚህ ይረዳሉ**)
8. **የምስክርነት ማስረጃ** (**አንድ ፍሬ ነገር ስለመፈሙ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ያወቀ ማንኛውም ሰው የሚሰጠው የምስክርነት ቃል**)
9. **የባለሞያ ምስክርነት ማስረጃ** (**በባለሞያዎች የሚሰጥ ሞያዊ ምስክርንት ቃል ለምሳሌ. ትራፊክ ፖሊስ፣ኦዲተር፣ጤና ባለሙያ…ወዘተ**)
10. **ዲጂታል ማስረጃ** (**በኮምፒዩተር ድራይቭ፣ ፍላሽ፣ ሞባይል እና መሰል የኤሌክትሮኒክ እቃዎች ላይ የሚገኝ ማስረጃ**)
11. **የሰነድ ማስረጃ** (**በሰነዶች ላይ ሰፍሮ የሚገኝ ማስረጃ**)
12. **ገላጭ ማስረጃ**(**አንድ ጉዳይ ስለመፈጸሙ የሚገልጽ ማናቸውም ማቴሪያል ለምሳሌ.ፎቶ፣ስእል፣ቪዲዮ….**)
13. **የባህሪ ማስረጃ** (Character evidence) (**አንድ ግለሰብ በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን ባህሪ የሚያሳይ ማስረጃ**)
14. **የልማድ ማስረጃ** (Habit evidence) (**ተጠርጣሪው ለአንድ ነገር በተደጋጋሚ ሲያሳይ የነበረውን ፍላጎት እና መልስ የሚያሳይ ማስረጃ**)
15. **የስሚ ስሚ ማስረጃ** (Hearsay evidence) (**ከአንድ ጉዳይ ጋር በተገናኘ በቀጥታ ሲነገር የነበረን ንግግር ባይሰማም በቀጥታ ከሰሙ ሰዎች ሰምቶ ይሄንኑ የሚገልጽ የምስክርነት ቃል**
16. **ማጠናከሪያ ማስረጃ** (Corroborating evidence)(**አንድ የቀረበ ማስረጃን የበለጠ ለማጠናከር የሚቀርብ ማስረጃ ነው**)
17. **የተከሳሹ ድርጊት ወንጀል አለመሆኑን፣ይቅርታ የሚያሰጥ መሆኑን ወይም ጥፋተኛ የማያሰኝ መሆኑን ለማስረዳት የሚቀርብ ማስረጃ**(Exculpatory evidence)

18. **ተቀባይነት ያለው ማስረጃ**(Admissible evidence) (**ህጋዊ ተቀባይነት ያለው ማስረጃ-ህጋዊ ሂደትን ተከትሎ የቀረበ ማስረጃ**)
19. **ተቀባይነት የሌለው ማስረጃ**(Inadmissible evidence) (**ህጋዊ ሂደትን ተከትሎ ያልቀረበ ማስረጃ**)
20. በቂ ያልሆነ ማስረጃ (Insufficient evidence) (**በማስረጃ ምዘና ሂደት የተያዘውን ጭብጥ ለማስረዳት በራሱ በቂ ያልሆነ ማስረጃ**) **የሚሉ ናቸው።**
21. **አግባብነት ያለው ማስረጃ** (relevant evidence) **ማረጋገጥ ለተፈለገው ፍሬ ነገር አግባብነት ያለው ማስረጃ የሚሉ ናቸው።**

ከዚህ ዝርዝር መረዳት እንደሚቻለው የማስረጃ አይነቶቹ የተከፋፈሉበት መሰረት እላይ እንዳነሳነው ወጥነት ያለው እና የተለያዩ ማስረጃ ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮች የሚገኙባቸውን ሁኔታ ፣ ለድርጊቱ ያላቸውን ቅርበት፣ ለፍርድ ቤት ሊቀርቡ የሚችሉበት መንገድ፣ ፍርድ ቤት ቀርበው ጉዳዩን ለማስረዳት ያላቸው አቅም፣ የማስረጃ አቀራረብ ህግን ተከትለው የተሰበሰቡ መሆናቸው እና መሰል ጉዳዮችን በማየት የተዘረዘሩ ናቸው ማለት ይቻላል።

ከነዚህ በአሁናዊው ወይም በጥንታዊው የማስረጃ አይነቶች ዝርዝር ውስጥ ከተካተቱት ማስረጃዎች የሰነድ ማስረጃ የዚህ ጽሁፍ ማእከላዊ ሀሳብ በመሆኑ ይህ የማስረጃ አይነት በይዘቱ ምን ምንን ሊያካትት ይችላል የሚለው ሀሳብ አከራካሪ ነው። ክፍፍሉም ፍጹም ሳይሆን በአንዱ የማስረጃ አይነት የሚካተተው ፍሬ ነገር በሌላኛው የማስረጃ አይነትም ሊካተት የሚችልባቸው ሁኔታዎች አሉ።

ስለዚህ ይህ የማስረጃ ክፍፍል ጉዳዩን የበለጠ ለመረዳት እንዲያስችል የሚደረግ ከመሆኑ ውጪ በህግ ደረጃ ሁሉም የማስረጃ አይነቶች አንድ የጋራ አላማ ያላቸው ናቸው እሱም አከራካሪ የሆኑ ፍሬ ነገሮች መኖር አለመኖራቸውን ወይም መፈጸም አለመፈጸማቸውን ማረጋገጥ ነው።

1.7. ሀሰተኛ ማስረጃ

በፍርድ አሰጣጥ ሂደት በጣም ከፍተኛ ችግር መበፍጠር እውነት እና ፍትህ እንዲዛባ በማድረግ የፍትህ ስርአቱ ተአማኒነት እንዳይኖረው፣ተግማችና ወጥ እንዳይሆን ከሚያደርጉ ችግሮች መካከል ሀሰተኛ ማስረጃ ግንባር ቀደሙ ችግር ነው። ከላይ የተዘረዘሩት የማስረጃ አይነቶች

ወደሀሰትነት ተቀይረው ወይም በሀሰት ተፈብርከው እየቀረቡ ተገቢ ያልሆኑ ውሳኔዎች እንዲሰጥ በማድረግ በፍትህ ስርአቱ ላይ አደጋ እየሆኑ መጥተዋል።

ማስረጃዎቹ በሀሰት የሚቀርቡበትን ሁኔታ ስናይ ሰዎች በስሜት ህዋሳቸው ያላዩትን ነገር የሌለውን አለ እያሉ ያለውን የለም እያሉ በቅጥፈት የምስክርነት ቃላቸውን የሚሰጡ ሲሆን ገላጭ እና ኤግዚቢት ማስረጃዎችን ከማይገናኙት ነገር ለማስመሰል በሀሰት አቀናብሮ ማቅርብ ሲሆን የሰነድ ማስረጃዎችን በተመለከተም በዋናነት እነዚህ ሰነዶች በሰው ልጅ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የሚዘጋጁ ወይም በቀላሉ በሀሰት ሊፈበረኩ እና አስረጂ ሆነው ሊቀርቡ ይችላሉ። በሌላ በኩል በእውነትነት የተዘጋጁትን የአስረጂዎች ይዘት በቀላሉ በመቀየር፣በመደለዝ ሰነዶቹ ሲዘጋጁ የነበራቸውን የመረጃ ይዘት እንዲቀየር በማድረግ በሀሰት ለተቀነባባረ የክስ ወይም መልስ ፍሬ ነገር አስረጂ ሆነው ይዘታቸውን ቀይረው እንዲቀርቡ ሲደረጉ ይስተዋላል።

በሀሰት ተቀነባብረው ከሚቀርቡ የማስረጃ አይነቶች አንዱ እና ዋነኛው የሆነው ሀሰተኛ ሰነድን በተመለከተ በቀጣዩ ክፍል በስፋት የምናየው ይሆናል።

1.8. ሀሰተኛ የሰነድ ማስረጃ

ሀሰተኛ ሰነድ ከአራቱ የማስረጃ አይነቶች አንዱ የሆነው የሰነድ ማስረጃ ላይ የሚፈጸም ወንጀል ነው።። ሀሰተኛ ሰነድ በመደበኛ የእንግሊዘኛ አጠራሩ Forgery ተብሎ የሚታወቅ ሲሆን diffense criminal የተሰኘ ድህረገጽ ባስቀመጠው መሰረት Forgery involves the making, altering, use, or possession of a false writing in order to commit a fraud. It can occur in many forms, from signing another person's name on a check to falsifying one's own academic transcript. When the subject of forgery is currency, it is also called counterfeiting.[8] ሲል ይገልጸዋል ትርጓሜውም ሀሰተኛ ሰነድ ማለት ለማጭበርበር በማሰብ ሀሰተኛ የሆነ የጽሁፍ ይዘት ያለውን ሰነድ ማዘጋጀት፣ ትክክለኛውን ጽሁፍ ይዘት መቀየር፣ በሀሰት የተዘጋጀውን ጽሁፍ መጠቀም፣ ወይም መያዝ ሲሆን የሌላን ሰው ስም አስመስሎ መፈረምን ሊያካትት ይችላል። የሀሰት ድርጊት የተፈጸመበት ሰነድ የገንዘብ ኖት ሲሆን ካውንተርፋይቲንግ (counterfeiting) ይባላል።

[8] https://www.criminaldefenselawyer.com/penalty-for-forgery.cfm lastely accessed on 23 December 2022

በተመሳሳይ ሁኔታ legal match የተሰኘ ድረ ገጽ በሰጠው ትርጉም መሰረት "Forgery is making, using, altering, or possessing a false document with the intent to commit fraud. Forgery can be the creation of a false document, or changing an authentic one.[9] ሲል ገልጾታል። ትርጉሙም እላይ ካነሳነው ጋር የሚቀራረብ ሲሆን ሀሰት የሆነ መረጃ ያለበትን ሰነድ ማዘጋጀት ፣መጠቀም፣መያዝ፣ሲሆን ይህ ድርጊት የሚፈጸመውም ዝም ብሎ ሳይሆን ተገቢ ያልሆነ ጠቅም ለማግኘት ወይም ማስገኘትን በማሰብ ነው። ከዚህም መረዳት የሚቻለው አንድ ሰው የሀሰተኛ ሰነድ ወንጀል ፈጽሟል ለማለት አራት መሰረታዊ ጉዳዮች መሟላት አለባቸው። እነሱም፡-

1. ሀሰተኛ የሆነውን ሰነድ ማዘጋጀት፣መቀየር፣መጠቀም ወይም ይዞ መገኘት፤

   አንድ ሰው ሀሰተኛ የሆነውን ሰነድ አዘጋጀ የሚባለው በራሱ እውቀት ወይም እራሱ በሚያዛቸው ሰዎች አማካይነት ሀሰተኛ መረጃ ያለበትን ሰነድ ካዘጋጀ ነው።

2. በሰነዱ ላይ ያረፈው ጽሁፍ ህጋዊ ውጤት ያለው ጽሁፍ ከሆነ፤

   አንድ ጽሁፍ ህጋዊ ውጤት ያለው ነው የሚባለው በሰነዱ ላይ ያረፈው ጽሁፍ የሌሎች ሰዎችን መብት እና ግዴታዎች ላይ ተጽኖ ማድረግ ሲችል ነው። ከዚህ ውጪ በህግ ፊት ተቀባይነት ለሌለው ግንኙነት ሲባል ለተደረገ ሀሰተኛ ጽሁፍ ከወንጀል ህግ አንጻር ሀሰተኛ ሰነድ መፍጠር ነው የሚያስብል አይደለም። ጽሁፉ የሚያደርሰው ተጽእኖ በመንግስት ወይም በግለሰብ ወይም በድርጅቶች ላይ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ የሌላን ሰው ፊርማ አስመስሎ በመፈረም በሰነዱ የተገኘው ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ተጎጂ የሆነው ድርጅት ወይም የመንግስት መስሪያ ቤት ሊሆን ይችላል ምክንያቱም በሀሰት የተዘጋጀው የቅጥር ደብዳቤ ቢሆን ቀጣሪው ድርጅት በዚሁ ደብዳቤ መሰረት ደሞዝ እና ጥቅማጥቅም ይከፍላል። ይሄም በመንግስት ወይም በግል ድርጅቱ(ቀጣሪው) ላይ ጉዳት ያመጣል። በዚሁ የቅጥር ደብዳቤ ላይ ያረፈው ጽሁፍ የቅጥር ውል ሲሆን ይህ ጽሁፍ ህጋዊ ውጤት ያለው ጽሁፍ ነው።

[9] https://www.legalmatch.com/law-library/article/forgery-laws.html#:~:text=White%20Collar%20Crime-,What%20is%20Forgery%3F,and%20by%20the%20federal%20government. lastely accessed on 24 December 2022

3. **ሰነዱ ላይ ያረፈው ጽሁፍ በሀሰት የተዘጋጀ መሆን አለበት-ሰነዱ ሲዘጋጅ የሌለውን ነገር እንዳለ እንዲሁም ያለን ደግሞ እንደሌለ አስመስሎ ከተዘጋጀ እና የሰነዱ ዋና ይዘት በሀሰት ተቀይሮ የቀረበ ከሆነ ነው።**
4. **ሰነዱ ለማታለል አላማ የተዘጋጀ ከሆነ ነው።**

ሀሰተኛ ሰነዱ ሲዘጋጅ የአዘጋጁ ዋነኛ አላማ በሰነዱ ሌላን ሰው አታለሎ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለራሱ ማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ማስገኘት ከሆነ ነው። ብዙውን ጊዜ በሀሰት የሚዘጋጁ ሰነዶች መብትን አለአግባብ የሚያጎናጽፉ ሲሆን ለምሳሌ ያክል ተደጋግመው በሀሰት የሚዘጋጁት የሚከተሉት ሰነዶች ናቸው።

- ***መታወቂያ፣የመንጃ ፈቃድ፣ፓስፖርት፣የትምህርት ማስረጃ*** (ID like driver's licenses or passports)
- **ቼኮች** (Checks)
- **የኑዛዜ ወረቀቶች** (Wills)
- **የመድሀኒት ማዘዣዎች** (Drug prescriptions)
- **የባለቤትነት ማረጋገጫ ወረቀቶች/ካርታዎች ፣ሊብሬዎች** (Deeds)
- **የአክሲዮን ወረቀቶች፣**(Stock certificates)
- **ውሎች** (Contracts)
- **የአእምሮ ፈጠራ ባለቤትነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬቶች** (Patents)
- **የአገር መከላከያ ሰነዶች** (Military documents)
- **የታሪክ ሰነዶች** (Historical documents)
- **የጥበብ ስራ ማረጋገጫዎች** (Works of art)
- **የሰነዶች ማረጋጋጫ ምስክር ወረቀቶች** (certificates of authentication)

እላይ ካስቀመጥናቸው መሰረታዊ ጉዳዮች አንጻር ሀሰተኛ ሰነድ የሚያዘጋጁ እና የሚጠቀሙ ሰዎች ብዙውን ጊዜ የሚያነሱት መከራከሪያ ሀሳብ ሰነዶቹን ሥንፈጠር ለ የማታለል ሀሳብ አልነበረንም፣የማወቅ እድሉም አልነበረንም፣ተገደን ነው ያዘጋጀነው ወዘተ የሚሉ ጉዳዮችን ያነሳሉ። እነዚህ መከራከሪያዎች ግን ተቀባይነት የሚኖራቸው በተለየ ሁኔታ ማስረጃ በማቅረብ ስለመገደዱ፣ለማጭበርበሪያነት ለመጠቀም አለመሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው። ከዚህ ውጭ ሀሰተኛ ሰነድ በማንኛውም ሁኔታ የሚያስቀጣ ወንጀል መሆኑ በተለያዩ አገራት የወንጀል ህግጋት ተደንግጎ ይገኛል።

ሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀትና መገልገል የሀገርን ኢኮኖሚ እንዲሁም የዜጎችን መብትና ጥቅም ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርስ የወንጀል ተግባር ነው። ሀሰተኛ ሰነዶች ዝግጅት በረቀቀና እውነተኛውን በሚመስል መንገድ የሚፈፀም በመሆኑ ይህን ከባድ ወንጀል ለመከላከልና አጥፊዎችን ለመቅጣት ብሎም ህብረተሰቡ ከዚህ ወንጀል እራሱን እንዲጠብቅ ግንዛቤ መፍጠር ያስፈልጋል።

የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 2(4) እና አንቀጽ 23 መሰረት ሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀቱ በመንግስታዊና ህዝባዊ ድርጅቶች ሰነዶች ላይ የሚፈፀም ከሆነ በሙስና ወንጀል የሚያስጠይቅ ነው። መንግስታዊ ሰነድ ሲባል የሚኒስቴር መስሪያ ቤት ወይም የክልል ቢሮዎችና በየደረጃው ያሉ አስተዳደር መስሪያ ቤቶች የወጡ በማስመሰል የሚዘጋጅ ሲሆን ለምሳሌ የንግድ ወይም ኢንቨስትመንት ፈቃድ ወረቀቶች፣ የይለፍ ወረቀቶች፣ የብቃት ማረጋገጫዎች፣ የስራ ፈቃድ ወረቀቶች፣ የስራ ልምድ፣ የክፍያ ማዘዣዎች፣ የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ ወይም ሊብሬዎች፣ ወዘተ የሚያካትት ነው። የህዝባዊ ድርጅቶች ሰነድ ደግሞ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ወይም ተቋማት ሰነዶች ለምሳሌ የመጋዘን ደረሰኝ፣ የእቃ ማውጫ ፈቃድ፣ የትምህርት ማስረጃ፣ የባንክ ክፍያ ሰነዶች እና መሰል በእነዚህ ተቋማት የሚሰጡ ሰነዶችን የሚመለከት ነው። እነዚህ ሰነዶች በአግልግሎት ሰጪዎች ወይም በተገልጋዮች በሀሰት ሊዘጋጁ ይችላሉ። ሰነዶችን ማዘጋጀትና መገልገል የሚያስከትለውን የህግ ተጠያቂነት በክፍል ሁለት በዝርዝር ይቀርባል።

ክፍል ሁለት

2. ሀሰተኛ የሰነድ ማስረጃ ማዘጋጀት እና መገልገል የሚያስከትለው የህግ ተጠያቂነት

ከሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀት እና መገልገል ጋር በተገናኘ በፈጻሚዎች ላይ የተለያየ አይነት የህግ ተጠያቂነት ያለ ሲሆን እሱም ፍትሐብሔር፣ የወንጀል እና አስተዳደራዊ ተጠያቂነት ናቸው። እነዚህን ተጠያቂነቶች በሚቀጥሉት ክፍሎች የምናያቸው ሲሆን በማስቀደም የወንጀል ተጠያቂነቱን እናያለን። በመቀጠልም ስለሚኖር ፍትሐብሔር እና አስተዳደራዊ ተጠያቂነትን የምንዳስስ ይሆናል።

2.1. የወንጀል ተጠያቂነት በጠቅላላው

የወንጀል ተጠያቂነት አንድ ሰው ቀድሞ በወጣ የወንጀል ህግ መሰረት አታድርግ ተብለው የተደነገጉ ድርጊቶችን ማድረግ እና መፈጸም ያለባቸውን ድርጊቶች ያለመፈጸም ነው። ይህ ሀሳብ በ1996 የወጣው የወንጀል ህግ አንቀጽ 23 ላይ ተደንግጎ ይገኛል። በዚሁ ድንጋጌ መሰረት አንድ ሰው ወንጀል ፈጽሟል የሚባለው በወንጀልነት የተደነገገውን ድርጊት ለመፈጸም የሞራላዊ ፣ ግዙፋዊ እና ህጋዊ ፍሬ ነገሮችን አሟልቶ የፈጸመው ከሆነ ብቻ ነው። የወንጀሉ ሞራላዊ ክፍል ወንጀለኛው የወንጀል ድርጊት ወይም ያለማድረግን የፈጸመው ስለ ድርጊቱ አስቀድሞ ግንዛቤ ኖሮት የድርጊቱን ውጤት በመቀበል ወዶ እና ፈቅዶ ከፈጸመው መሆኑን ከወንጀል ህጉ አንቀጽ 57 መረዳት ይችላል። በተጨማሪም ወንጀል ፈጻሚው የወንጀል ድርጊት ወይም ያለማድረግን የፈጸመው ድርጊቱ የሚያስከትለውን ውጤት ፈልጎ ብቻ ሳይሆን በህግ በተደነገገ ጊዜ ማድረግ የሚገባውን ጥንቃቄ ባለማድረግ ማወቅ እየተገባው፣ ወይም አውቆ ነግር ግን ውጤቱን ከወዲሁ ሳይቀበል የመጣው ይምጣ በማለት በታወቀ ቸልተኝነት ስሜት ውስጥ ሆኖ ለሚፈጽመው የወንጀል ድርጊትም ተጠያቂ ሊሆን እንደሚችል ከወንጀል ህጉ አንቀጽ 59 ንባብ በግልጽ መገንዘብ ይቻላል።

ሁለተኛው የወንጀል ፍሬ ነገር ግዙፋዊነት ሲሆን ይሄውም የተባለው የወንጀል ድርጊት በተግባር ተፈጽሞ መገኘቱ ነው። አንድ የወንጀል ድርጊት ተፈጸመ የሚባለው መቼ ነው? የሚለውን ሀሳብ ብናነሳ ወንጀለኛው ወንጀሉን ለመፈጸም ተሰናድቶ ቢያንስ ከሞከረው ወይም በሚሞክርበት ጊዜ መሆኑን ህጉ በአንቀጽ 27 ላይ ስለሙከራ በደነገገበት ላይ አስቀምጦት ይገኛል። ነግር ግን በሃገር ሰላም እና ደህንነት፣ በህገመንግስት እና ህገ መንግስታዊ ስርአት ላይ

የሚፈጸሙ እና መሰል ከባድ ወንጀሎችን ለመፈጸም መሰናዳት በራሱ በቂ ሆኖ ወንጀሎቹ ባይሞከሩም በህግ የሚያስጠይቅ መሆኑ ከወንጀል ህጉ አንቀጽ 26 ፣238 እና ቀጥሎ ያሉ ድንጋጌዎች ብሎም ከልዩ ልዩ አዋጆች የወንጀል ድንጋጌዎች ይዘት መረዳት ይቻላል።

ሶስተኛው የወንጀል ፍሬ ነገር ህጋዊ ፍሬ ነገር ነው። ይሄውም የተፈጸመው ድርጊት ታሰቦም ሆና በቸልተኝነት ይፈጸም በዚህ ብቻውን ወንጀል ሊሆን አይችልም። ከወንጀል ህግ ህጋዊነት መርህ እንደምንረዳው ድርጊቱ በህጉ ወንጀል ነው ተብሎ በግልጽ መደንገግ አለበት። በተጨማሪም ድርጊቱ ብቻ ሳይሆንም የተፈመው ድርጊት የሚያስከትለው ተመጣጣኝ ቅጣትም ከድርጊቱ መፈጸም በፊት በዝርዝር መደንገግ አለበት። በ1996 ዓ.ም የወጣው የወንጀል ህግ ልዩ ክፍል እነዚህን ዝርዝር የወንጀል ተግባሮች ዘርዝሮ አስቀምጧል። በተጨማሪም በወንጀል ህጉ አንቀጽ 3 መሰረት በዚህ ህግ ያልተሸፈኑ ወንጀሎች ላይ ልየ ልዩ አዋጆች አማካይነት የወጡ የወንጀል ድንጋጌዎች ይሄንኑ ህጋዊነት መርህ በመከተል ዝርዝር ወንጀሎችን ደንግገው ይገኛሉ።

ከሀሰተኛ ሰነድ ጋር በተገናኘም በወንጀል ህጉ አንቀጽ 375 እና ቀጥሎ ባሉ ድንጋጌዎች በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 23 መሰረት በመንግስታዊ እና ህዝባዊ በሰነዶች ላይ የሚደረግ የወንጀል ድርጊት እንደሚያስጠይቅ ደንግገው ይገኛሉ። የሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀት እና መገልግል የወንጀል ተጠያቂነትን በቀጣይ ክፍል በስፋት የምናየው ይሆናል።

2.2. የሀሰተኛ የሰነድ ማስረጃ ማዘጋጀት እና መገልገል የሚያስከትለው የወንጀል ተጠያቂነት

በአገራችን የወንጀል ፍትህ ስርአት ሀሰተኛ ማስረጃን በተመለከተ የሚያስጠይቁ በሁለት የሚከፈሉ ድርጊቶች አሉ። እነሱም የመጀመሪያው ሀሰተኛ ሰነድን ማዘጋጀት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ሌላ ሰው ወይም ድርጅት ባዘጋጀው ሀሰተኛ ሰነድ መገልገል ነው።

ሀሰተኛ ሰነድ መፍጠር፣በእውነት የተዘጋጁትን ሰነዶች ወደ ሀሰትነት መለወጥ እና በዚሁ በሀሰት በተለወጠ ወይም በተዘጋጀ ሰነድ መገልገል የሚያስከትለውን የወንጀል ተጠያቂነት ስናይ በመጀመሪያ በወንጀል ህጉ ስለጉዳዩ የተካተቱትን ድንጋጌዎች የምናይ ሲሆን ቀጥሎም የወንጀል ድንጋጌ የያዙ የተለያዩ አዋጆች ስለ ሀሰተኛ ሰነድ መፍጠር እና መገልገል የደነገጉትን የምናይ ይሆናል።

2.3. የሀሰተኛ የሰነድ ማስረጃ ማዘጋጀት እና መገልገል በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.የወንጀል ህግ

በ1996ዓ.ም. የወጣው የወንጀል ህግ በመጽሀፍ አራት በህዝብ አመኔታ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ስር ከተዘረዘሩ ወንጀሎች መካከል ሀሰተኛ ሰነዶችን መፍጠር፣ሰነዶችን ወደ ሀሰት መለወጥና ማጥፋት ይገኙበታል። በዚህ ርእስ ስር የተዘረዘሩ ወንጀሎችም ከአንቀጽ 375 እስከ 384 ድረስ ያሉ ሲሆን እነሱም፡-

- በግዙፍ የሚፈጸም ሀሰት
- ረቂቅ በሆነ ሁኔታ የፈጸም ሀሰት
- በሰተኛ ነሰድ መገልገል
- መንግስታዊ ወይም ወታደራዊ ሰነዶችን አስመስሎ ማዘጋጀት
- ሰነዶችን ማጥፋት
- መንግስታዊ ወይም ወታደራዊ ሰነዶችን ማጥፋት
- የንግድ ወይም ተላላፊ የዋስትና ሰነዶችን ወደ ሀሰት መለወጥና ማጥፋት
- የህዝብ ማመላለሻ አገልግሎት ወረቀቶችንና የማጓጓዣ ወረቀቶችን ወደሀሰት መለወጥና በነዚሁ መገልገል የሚሉ ናቸው።

ሌላው ከሀሰተኛ ሰነድ ጋር በተገናኘ የተደነገጉት ወንጀሎች በወንጀል ህጉ እራሱን በቻለ ክፍል ከአንቀጽ 385 ጀምሮ እስከ 390 ድረስ የተደነገጉት በምስክር ወረቀቶች ላይ የሚፈጸሙ የሀሰት ወንጀሎች ናቸው። እነዚህም፡-

- ሀሰተኛ ምስክር ወረቀቶች
- ሀሰተኛ የሆነ ኦፊሴላዊ ምስክርነት በማጭበርበር ማግኘት
- ሀሰተኛ የህክምና ምስክር ወረቀቶች
- ሀሰተኛ የቃል አሰጣጥ እና መዝገባ
- ሀሰተኛ ሰነዶችን ለማዘጋጀት የሚያገለግሉ መሳሪያዎች እና መስሪዎችን መያዝ ፣ ማጓጓዝ እና መገልገል፣ ወዘተ የሚሉ ናቸው።

ከነዚህ ወንጀሎች መካከል በግዙፍ የሚፈጸም ሀሰት የሚለውን ስናይ ማንም ሰው የሌላውን መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት በማሰብ ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ተገቢ ያልሆነ ማናቸውንም መብት ወይም ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ፡-

- ✓ ህጋዊ ክርክሮች ሲካሄዱ በማስረጃነት የሚቀርቡ ፣አንድን ፍሬ ነገር ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ወይም የሚያረጋግጡ የሚመስሉ እንደ ጽሁፍ ፣ ሌሎች ሰነዶች ወይም ግዙፍ ነገሮች የማሰሉትን መፍጠር ፤
- ✓ ሐሰተና ሰነድ ለማዘጋጀት በሌላ ሰው የጣት ፊርማ ምልክት ወይም ማህተም መጠቀም ፤
- ✓ እውነተኛውን ጽሁፍ በመለወጥ ወይም በመደለዝ በሀሰተኛ ፊርማ በእጅ በተደረገ ምልክት ወይም በጣት ፊርማ፣ በማህተም ወይም የሌለን ስልጣን ወይም ችሎታ እንዳለው አስመስሎ በመፈረም ሀሰተኛ ነሰድ መፍጠር ፤
- ✓ አንድን ሰነድ በተለይም የፈራሚውን ስም ወይም ፊርማ ወይም የሰነዱን ይዘት ፤ አሃዝ፣ ፍሬ ነገር ወይም ዝርዝር መግለጫ በሙሉ ወይም በከፊል በመለወጥ ፤ በማሻሻል ፣ በመቀነስ፣ በመጨመር ወይም በማጥፋት ወደ ሀሰተኛነት መለወጥ ፤

ከ3 ወር በማያንስ ቀላል እስራት ወይም ነገሩ ከባድ ሲሆን ከ10 አመት በማይበልጥ ጽ እስራት ያስቀጣል።

ሌላው ትኩረት የሚሻው የህጉ አንቀጽ 378 ላይ የተደነገገው በሀሰተኛ ሰነድ መገልገል ወንጀል ነው። በዚሁ ድንጋጌ መሰረት ማንም ሰው በሀሰት በተዘጋጀ ወይም ወደ ሀሰት በተለወጠ ሰነድ እያወቀ የተገለገለበት እንደሆነ በአንቀጽ 375 መሰረት ከ3 ወር በማያንስ ቀላል እስራት ወይም ነገሩ ከባድ ሲሆን ከ10 አመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ወንጀል መሆኑን ነው።

በተጨማሪም ጥቅም ወይም መሻሻልን ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ ተገቢ መብት ለማስገኘት የሚችሉ ፅሁፎችን፣ ግላዊ ሁኔታን የሚገልፁ ማስረጃዎችን ወይም ምስክርነትን ማስረጃዎችን ወይም ማናቸውንም አይነት ጉዳይ የሚመለከቱ የምስክርነት ማረጋገጫ ሰነዶችን ወደ ሀሰተኛነት የለወጠ ወይም አስመስሎ የሰራ ወይም እያወቀ ይህን የመሰለውን ሰነድ እንዲገለገልበት ለሌላ ሰው መስጠት በወንጀል ህጉ አንቀፅ 385 መሰረት በቀላል እስራት ወይም መቀጮ ያስቀጣል። ይህ ሰነድ የግል ጉዳይን የያዘ እንደሆነ ከአንድ አመት ባልበለጠ እስራት፣ ወይም ሰነዱ ህዝባዊ ባህሪ ያለው ሆኖ እንደመታወቂያ ወረቀት ወይም የልደት ምስክር ወረቀት ወይም የችግርተኛነት፣ የመልካም ጠባይ፣ የብቁነት ወይም ብቁ አለመሆን ማረጋገጫ ምስክርነት ወይም የህዝብ መዝገብ ወይም መቆጣጠሪያ ቅጂ እንደሆነ ከሶስት ወር በማያንስ እስራት ያስቀጣል።

በሌላ በኩል ወንጀሉን የፈፀመው እነዚህን ሰነዶች እንዲያዘጋጅ፣ እንዲያስቀምጥ፣ እንዲጠብቅ ወይም እንዲሰጥ ሀላፊነት በተሰጠው የመንግስት ሰራተኛ እንደሆነ እና ይህን ወንጀል ያደረገው በሌላ ሰው መብት ላይ ጉዳት ለማድረስ ሳያስብ እንደሆነ ከስድስት ወር እስከ አምስት አመት በሚደርስ እስራት ወይም በመቀጮ ወይም በሁለቱም ያስቀጣል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ማንኛውም ሀኪም፣ የጥርስ ሀኪም፣ የመድሀኒት ቅመማ ባለሙያ፣ የእንስሳት ሀኪም፣ አዋላጅ ወይም በህክምና ሙያው ህክምናን በሚመለከት የምስክር ወረቀት ለመስጠት መብት ያለው ማንኛውም ሌላ ሰው የምስክር ወረቀት ስራ ላይ እንደሚውል እያወቀ ለተቀባዩ ሰው የማይገባ ጥቅም ለማስገኘት የሚችል ወይም የሌላውን ሰው ህጋዊ ጥቅም የሚነዳ ሀሰተኛ የህክምና ምስክር ወረቀት አዘጋጅቶ ፅፎ የሰጠ በወንጀል ህግ አንቀፅ 387 መሰረት በቀላል እስራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል። ይህ ወንጀል በመንግስት ሰራተኛ ከተፈፀመ ወይም ወንጀሉ በስጦታ ወይም በሌላ ጥቅም የተፈፀመ ከሆነ ቅጣቱ ከአስር እስከ አስራ አምስት አመት እስራት ይደርሳል። በመጨረሻም ማንም ሰው ህገ ወጥ በሆነ መንገድ ሊገለገልባቸው በማሰብ ኦፊሴላዊ ፅሁፎችን፣ የምስክር ወረቀቶችን፣ ዲፕሎማዎችን ወይም ሰነዶችን ወደ ሀሰተኛነት ለመለወጥ ወይም በሀሰት ለመፍጠር የሚያገለግሉ መሳሪያዎችንና መስሪያዎችን ወይም ቁሳዊ ነገሮችን የሰራ፣ በእጁ ያስገባ፣ የያዘ፣ የሰጠ ወይም ለሽያጭ ወይም ለስጦታ ያቀረበ እንደሆነ በአንቀፅ 390 መሰረት ከአምስት አመት በማይበልጥ እስራት እና በመቀጮ ይቀጣል።

በወንጀል ህጉ በሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀቱ እና መገልገሉ በተጨማሪነት በወንጀል ህጉ አንቀጽ 692 መሰረት የሚፈጸም የአታላይነት ወንጀል ሀሰተኛ ሰነድ በማዘጋጀት ወይም በሀሰት የተዘጋጅን ሰነድ በመጠቀም የራሱን ማንነት በመደበቅ የሌላውን ሰው የተሳሳተ እምነት እና ግምት በመጠቀም በማድረግ ባለማድረግ ሌላውን ሰው አታሎ ተጎጂው የራሱን ወይም የሌላ ሰው ጥቅም የሚነዳ ድርጊት እንዲፈጽም ካደረገ በቀላል እስራት ወይም ነገሩ ከባድ ሲሆን ከ5 አመት በማይነልጥ ጽኑ አስራት እና መቀጮ የሚስቀጣ ወንጀል ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 675 መሰረት ተጠርታሪው ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ብልጽግና ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ የተጣለብትን እመነት ወደጎን በመተው ለአንድ ለተወሰነ አለማ የተሰጠውመን ዋጋ ያለውን ንብረት የራሱ ወይም የሌላ ሶስተኛ ወገን ለማድረግ ሀሰተኛ ነሰድ ካዘጋጀ ወይም በሌላ ሰው የተዘጋጀውን ሀሰተኛ ሰነድ አገልግሎት ላይ ካዋለ እንደነገሩ ሁኔታ በቀላል እስራት ወይም ከ5 አመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል።

በሰነዶች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ከላይ የዘረዘርናቸው ብቻ አይደሉም። በሌሎች አዋጆች የተደነገጉትን ወንጀሎች በሚከተለው ከፍል እናያለን።

2.4. ሀሰተኛ የሰነድ ማስረጃ ማዘጋጀት እና መገልገል በልዩ ልዩ አዋጆች

በወንጀል ህጉ ላይ ሀሰተኛ ሰነድን ማዘጋጀት እና መገልገልን የተመለከቱት ወንጀሎች ተፈጻሚነታቸው በመንግስታዊና ህዝባዊ ድርጅት ሰነዶችን ላይ በሚፈጸሙ ወንጀሎች ሳይሆን ከዚህ ውጪ ባሉት እና በእለት ተእለት የኑሮ እንቅስቃሴ የምንጠቀምባቸውን ግላዊ ሰነዶችን በሀሰተኛ መንገድ ማዘጋጀትና መገልገል በወንጀል የሚያስጠይቅበት ሁኔታ ነው።

ሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀቱ እና መጠቀሙ በመንግስት ድርጅቶች፣በመንግስት የልማት ድርጅቶች እና በህዝባዊ ድርጅት ሰነዶች ላይ በሚፈጸምበት ጊዜ ወንጀሉ የሙስና ወንጀል ሲሆን ተፈጻሚነት የሚኖረውም የወንጀል ህጉ ሳይሆን የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ የወጣው አዋጅ ቁጥር 881/2007 ይሆናል።

በዚሁም መሰረት ማንኛውም ሰው፡-

- የሌላውን ሰው መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ተገቢ ያልሆነ ማናቸውንም መብት ወይም ጥቅም ለማስገኘት በማሰብ፤
- አንድ ፅሁፍ፣ መዝገብ ወይም ማንኛውም ሰነድ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት በማስመሰል ያዘጋጀ ወይም የፈጠረ፤
- በመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅት መዝገብ፣ ፅሁፍ ወይም ሰነድ የሰፈረን እውነተኛውን ፅሁፍ በመለወጥ ወይም በመደለዝ፣ በሀሰተኛ ፊርማ፣ በእጅ በተደረገ ምልክት ወይም በጣት ፊርማ፣ በማህተም ወይም የሌለውን ስልጣን ወይም ችሎታ እንዳለው አስመስሎ በመፈረም ሀሰተኛ ሰነድ የፈጠረ እንደሆነ፤
- አንድን የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰነድ በተለይ የፈራሚውን ስም ወይም ፊርማ ወይም የሰነዱን ይዘት፣ አሃዝ፣ ፍሬ ነገር ወይም ዝርዝር መግለጫ በሙሉ ወይም በከፊል በመለወጥ፣ በማሻሻል፣ በመቀነስ ወይም በመጨመር ወይም በማጥፋት ወደ ሀሰተኛነት የለወጠ ወይም ማናቸውንም ሀሰተኛ ፍሬ ነገር ያስገባ ወይም እንዲገባ ያደረገ እንደሆነ፤

በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 23 መሰረት ከሶስት አመት እስከ አስር አመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ያስቀጣል።

ሌላው መገንዘብ የሚገባን ጉዳይ የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 23 (4) መሰረት በወንጀል የሚያስጠይቀው ሀሰተኛ ሰነዶችን ማዘጋጀት ብቻ ሳይሆን ይዞ መገኘትና መገልገል ጭምር ሲሆን በዚህም መሰረት ወደ ሀሰት የተለወጠ ወይም በሀሰት የተዘጋጀ ሰነድ በቤቱ፣ በተሽከርካሪው፣ በኪሱ ወይም በማንኛውም አግባብ በቁጥጥሩ ስር የተገኘ እንደሆነ በአንቀጽ 23 (1) መሰረት ከሶስት አመት እስከ አስር አመት በሚደርስ ፅኑ እስራት። በተጨማሪም ማንኛውም ሰው ወደ ሀሰት በተለወጠ ወይም በሀሰት በተዘጋጀ ሰነድ እያወቀ የተገለገለበት እንደሆነ በተመሳሳይ ይቀጣል።

በተጨማሪም የዚህ ወንጀል አፈፃፀም በሚከተለው ሁኔታ ሊከብድ የሚችል ሲሆን ይኸውም ሰነዶቹን እንዲያዘጋጅ፣ እንዲመዘግብ እንዲጠብቅ ወይም ከነዚሁ ውስጥ ቅጂዎችን እንዲሰጥ ሀላፊነት በተሰጠው የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ እንደሆነ ወይም ሰነዱን በመገልገል የተገኘው ጥቅም ከፍተኛነት ወይም በግለሰብ፣ በመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ወይም በህዝብ ጥቅም ላይ ያደረሰው ጉዳት ከፍተኛ እንደሆነ ቅጣቱ ከአምስት አመት እስከ ሀያ አምስት አመት የሚደርስ እስራት ያስቀጣል።

በሙስና ወንጀሎች ልዩ ስነስርአት አዋጅ 434/1993(በአዋጅ 882/2007 እንደተሻሻለው) አንቀጽ 4 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት የሙስና ወንጀሎች ከ10 አመት ጽኑ እስራት በላይ የሚያስቀጡ ሆነው በተደነገጉበት ጊዜ ተከሳሽ በዋስ የመውጣት መብቱ በህግ የተገደበ መሆኑን እና በእስር ሆኖ ጉዳዩን የሚከታተል መሆኑን ማወቅ ይገባል። ሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀቱም ሆነ መገልገሉ እላይ በተገለጸው አግባብ ከ10 አመት ጽኑ አስራት በላይ ሊያስቀጣ የሚችልበት ሁኔታ ካለ ዋስትናው በዚሁ ልዩ የስነስርአት እና የማስረጃ አዋጅ መሰረት የተከለከል ነው።

በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 ላይ የተደነገገው አንደተጠበቀ ሆኖ ሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀቱ ወይም መገልገሉ ወንጀል የሳን ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ በሚሰጣቸው በብሄራዊ መታወቂያዎች፣የልደት ፣የጋብቻ እና መሰል ሰነዶች ላይ ከተፈጸመ በወሳኝ ኩነት ምዝገባ እና ብሄራዊ መታወቂያ አዋጅ ቁጥር 760/2004 አንቀጽ 66 መሰረት እንደ ወንጀሉ አፈጻጸም እና የደረሰው ጉዳት መጠን እስከ 25 አመት በሚደርስ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ወንጀል ነው።

በሌላ በኩል ከግብር አከፋፈል ጋር በተያያዘ ማንኛውም ሰው ሆን ብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት ለገቢዎች ሚኒስቴር የተሞከበረበሩ ሰነዶችን ያቀረበ እንደሆነ በፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ 983/2008 አንቀፅ 118 መሰረት ከሶስት እስከ አስራ አምስት አመት በሚደርስ እስራት ይቀጣል። በአንቀፅ 119 መሰረት ደግሞ እነዚህን የተሞከበረበሩ ደረሰኞችን ያዘጋጀ፣ ያተመ፣ የሸጠ ወይም ያሰራጨ ወይም የተጠቀመ ከሰባት አመት እስከ አስር አመት በሚደርስ እስራት ይቀጣል። የዚህን ወንጀል አፈፃፀም ለመከላከል ሲባል የተደነገገ ሌላ ጥፋት ሀሰተኛ ደረሰኞችን ለመስራት፣ ለማዘጋጀት ወይም ለማተም የሚያገለግል ማሽን፣ መሳሪያ ወይም ሶፍትዌር የያዘ፣ የሸጠ፣ ያከራየ ወይም በሌላ መንገድ ያቀረበ ማንኛውም ሰው ከአስር እስከ አስራ አምስት አመት እስራት እንደሚቀጣ በህጉ መደንገጉ ነው። በተመሳሳይ እነዚህን ሀሰተኛ ደረሰኞችን የያዘ፣ ያስቀመጠ፣ ለሽያጭ ያመቻቸ ወይ ሀሰተኛ ደረሰኞችን ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደረገ ከሶስት እስከ አምስት አመት እስራት ይቀጣል።

ከጉምሩክ መንግስታዊ ስራዎች ጋር በተያያዘ ማንኛውም ሰው በጉምሩክ ኮሚሽን ላይ ጉዳት ለማድረስ ወይም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ ኮሚሽኑ የሚጠቀምበትን ቅፅ፣ ማህተም፣ መታወቂያ፣ አርማ፣ የጉምሩክ ማሽጊያ ወይም ማናቸውም ሰነድ ወይም ምልክት ወደ ሀሰተኛነት የለወጠ ወይም አስመስሎ የሰራ ወይም ይህንኑ ያከፋፈለ፣ የተጠቀመ ወይም ለመጠቀም የሞከረ ወይም ለጉምሩክ ስነ ስርአት የሚቀርቡ ሰነዶችን የሰረዘ፣ የደለዘ፣ የፋቀ ወይም አስመስሎ የሰራ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀፅ 167 እና በጉምሩክ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ 1160/2011 አንቀፅ 169(4) መሰረት ከአምስት እስከ አስር አመት እስራት ይቀጣል።

በሰዎች መነገድ እና ሰዎችን በህገወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀል ጋርም በተገናኘ ሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀትም ሆነ መጠቀም በወንጀል የሚያስጠይቅ ተግባር ነው። በአዋጅ ቁጥር 1178/2012 አንቀጽ 10 መሰረት ገንዘብ ወይም ቁሳዊ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ ሰውን በህገወጥ መንገድ ድምበር ለማሻገር አላማ እንዲውል ሀሰተኛ የጎዞ ወይም የማንነት ሰነድ ማዘጋጀት፣ይዞ መገኘት፣ማቅረብ ወይም ማስተላለፍ ከ አምስት አመት እስከ አስራ አምስት አመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር አስር ሺ እስከ ሀምሳ ሺ ድረስ በሚደርስ መቀጮ ያስቀጣል።

በአጠቃላይ ከላይ ከተመለከቱት የሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀትና መገልገል ወንጀሎች ሰፊ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባና ህብረተሰቡ ከእነዚህ ወንጀሎች እራሱን ማራቅና መጠበቅ ያስፈልጋል።

እነዚህ ወንጀሎች በሀገርና በህብረተሰቡ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርሱ ሲሆን የዜጎችን መብትና ጥቅም በማጭበርበር የሚያሳጡ ናቸው። በህግም የሚያስከትሉት ተጠያቂነት ሰፊና ከባድ ነው። ስለሆነም ሀሰተኛ ሰነዶች ከማዘጋጀት፣ እንዲዘጋጅ ከማድረግ፣ ይዞ ከመገኘት፣ ከመገልገል፣ ሀሰተኛ ሰነድ መስሪያ መሳሪያዎችን ይዞ ከመገኘት መቆጠብ ያስፈልጋል። በተጨማሪም እንዲህ ያለ ጥፋት መፈፀሙን ስናስተውል ለህግ አስከባሪ አካላት ማሳወቅ እና ተጠያቂነት እንዲኖር ለማድረግ መተባበር ያስፈልጋል።

የፍትሐብሔር ተጠያቂነት

2.5. ፍትሐብሔር ተጠያቂነት በጠቅላላው

ከሀሰተኛ ሰነዶች ተጠያቂነት ጋር ተያይዞ የሚነሳው ሌላው ጉዳይ የፍትሐብሔር ተጠያቂነት ነው። ከሀሰተኛ ሰነድ መፍጠር እና መገልገል ጋር ተያይዞ ስለሚኖር የፍትሐብሔር ሃላፊነትን ለመረዳት ያስችለን ዘንድ ስለ የፍትሐብሔር ሀላፊነት ምንነት በጥቅሉ ለማየት እንሞክራለን።

የፍትሐብሔር ተጠያቂነት ሲባልም አንድ ሰው ወደ ጎን ከሌላ ሰው ወይም ህጋዊ ሰውነት ያለው ድርጅት ጋር እና ወደላይ ከመንግስት ተቋማት ጋር ባለው ግንኙነት ህጋዊ ውጤት ያላቸውን ግንኙነት በማድረጉ እና በዚህም ያልተወጣው ግዴታ ወይም ሀላፊነት ካለ ይሄንኑ ሀላፊነት ተገዶ እንዲፈጽም ወይም እሱ ሀላፊነቱን ባለመወጣቱ ምክንያት በሌላው ሰው ወይም ድርጅት ላይ ለደረሰው ጉዳት ኪሳራ እንዲከፍል የሚገደድበት የህግ ተጠያቂነት ነው። እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ሃለፊነቱን ያልተወጣው ሰው ወይም ድርጅት ልክ እንደ ወንጀል ቅጣት ነጻነትን በሚያሳጡ የእስራት ቅጣት ወይም ወንጀል በመፈጸሙ ለመንግስት ገቢ የሚሆን የገንዘብ መቀጮ የሚቀጣበት የቅጣት አይነት አለመሆኑን ነው። ይልቁንም መታሰሩ ወይም መቀጮ ለመንግስት ከመክፈል በተጨማሪ ለተጎጂው ግለሰብ ወይም ድርጅት በወንጀሉ ምክንያት ለደረሰበት ጉዳት ማካካሻ የሚከፈል የገንዘብ ካሳ ነው። በሌላ በኩል በውል የተመሰረተ ህጋዊ ግንኙነት ባይኖርም ይህ ሰው እንደ አንድ ምክንያታዊ ሰው ማድረግ የሚገባውን ባለማድረጉ ወይም ማድረግ የማይገባውን በማድረጉ፣ በእሱ ይዞታና ባለቤትነት ስር ባለ ማናቸውም ንብረት ምክንያት ሌላው ሰው ላይ ጉዳት ከደረሰ አለያም አሱ በሚያስተዳድራቸው ህጋዊ ተጠያቂነት በማይኖርባቸው ሰዎች ጥፋት ምክንያት ሌላ ሶስትኛ ሰው ላይ ለደረሰ ጉዳት ተጠያቂ ሆኖ ካሳ እንዲከፍል የሚገደድበት የህግ መሰረት ነው።

በዚሁ መሰረት በአገራችን የፍትህ ስርአት የፍትሐብሔር ተጠያቂነት የሚቋቋምባቸወን የህግ መሰረት ስናይ አንድ ሰው የፍትሐብሔር ተጠያቂነት ሊኖረው የሚችለው በውል እና ከውል ውጭ በሚኖር ሀላፊነት ነው። ከነዚህ ውጪ አለአግባብ መበልጸግን በሚመለከትም በህጉ የተቀመጡ ሁኔታዎች ሲሟሉ የፍትሐብሔር ተጠያቂነት ሊያስከትሉ እንደሚችሉ በህጉ ተገልጸ ይገኛል። ከሀሰተኛ ሰነድ ጋር ተያይዞ ላለ የፍትሐብሔር ሀላፊነት ለመረዳት ያስችለን ዘንድ ከውል እና ከውል ውጪ የሚመጣን የፍትሐብሔር ሀላፊነት በአጭሩ እንደሚከተለው ለመቃኘት እንሞክራለን።

በውል የሚመጣ የፍትሐብሔር ሀላፊነትን ስናይ አንድ ሰው ወይም የህግ ሰውነት ያለው ድርጅት ከሌላ ሰው ወይም ድርጅት ጋር በሚኖረው ግንኙነት የንብረትነት ባህሪ ያላቸውን ጉዳይ በተመለከተ ግዴታዎችን ለማቋቋም፣ለመለወጥ፣ለማስቀረት በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚደረግ ስምምነት መሆኑን በ1952 ዓ/ም የወጣው ከፍትሐብሔር ህግ አንቀጽ 1675 ድንጋጌ መረዳት ይቻላል። በዚሁ ውል የሚመጣን የፍትሐብሔር ሃላፊነት የመፈጸም ግዴታ እንዳለ ህጉ ይደነግጋል። በዚሁም መሰረት በፍትሐብሄር ህግ አንቀጽ 1731 ንኡስ አንቀጽ 1 ላይ እንደተደነገገው በህግ አግባብ የተቋቋሙ ውሎች ባቋቋሚቸው ሰዎች ላይ ህግ ናቸው። በዚህም አንድ ውል አስፈላጊውን ህጋዊ መስፈርት አሟልቶ እስከተቋቋመ ድረስ በተዋዋዮች መካከል ህግ ሆኖ ግዴታን ይጥላል። ይህም ማለት ተዋዋይ ወገኖች በገቡት ቃል መሰረት ውሉን ካልፈጸሙ ተጠያቂነት አለባቸው። ለዚህ ሁነኛው አገራዊ አገላለጽ 'የሰው ልጅ ቃሉ ማሰሪያው ነው!' የሚለው ብሂል ነው። በዚህም ውሉ እንደተዋዋሉት አልተፈጸመልኝም የሚል አካል ውሉን ከህጉ ጋር ጠቅሶ ግዴታውን ያልተወጣውን ተዋዋይ ወገን መክሰስ ይችላል። ፍርድ ቤቶችም ውሉ ህጋዊ ሂደትን ጠብቆ የተቋቋመ መሆኑን እና በቀረበው የክስ አቤቱታ መሰረት አንደኛው ተዋዋይ ወገን ግዴታውን እንደውሉ ያለመወጣቱን በግራቀኝ ክርክር እና ማስረጃ ካረጋገጠ በኋላ ግዴታውን ባል ተወጣው ተዋዋይ ወገን ላይ በፍትሐብሔር ህግ አንቀጽ 1790 እና ቀጥሎ ባሉ ድንጋጌዎች መሰረት ይህ ግለሰብ ወይም ድርጅት እንደየሁኔታው ውሉን ተገዶ እንዲፈጽም፣ ውሉ እንዲፈርስ ወይም በውሉ አለመፈጸም ምክንያት ለደረሰው ጉዳት ለሌላኛው ወገን ካሳ እንዲከፍል የሚሉ ውሳኔዎችን ሊያስተላልፍ ይችላል።

ሁለተኛውን የፍትሐብሔር ሀላፊነትን የሚያስከትለውን ሁኔታ ስናይ ከውል ውጪ የሚኖር ሀላፊነት ነው። በዚህ ፍትህብሔራዊ ሀላፊነት አንድ ሰው በሶስት ዋና ዋና ምክንያቶች ውል

ሳይኖር የፍትሐብሔር ሀላፊነት ሊኖርበት ይችላል። የሂውም በፍትሀብሄር ህጉ አንቀጽ 2026 መሰረት፡-

- ✓ እራሱ በሰራው ጥፋት ሌላ ሰው ላይ ጉዳት ከደረሰ ፣
- ✓ ሌላ ሰው ላይ ጉዳት ሊያደርስር የሚችል ስራ ከሰራ፣ ወይም በእጁ ባለ ንብረት ምክንያት ሌላ ሰው ላይ ጉዳት ከደረሰ ፣
- ✓ በህግ መሰረት ፣ እሱ የሚያስተዳድረው ሰው በሌላ ሰው ላይ ለፈጸመው ጠፋት፤

በሚሉ ምክንያቶች በህግ የፍትሐብሔር ተጠያቂነት አለበት።

በዚሁ ህግ አንቀጽ 2028 እና 2029 መሰረት በጥፋት ላይ የተመሰረቱ ተጠያቂነትን በተመለከተ አንድ ሰው አስቦ ወይም በቸልተኛነት ሌላ ሰው ላይ ጉዳት ካደረሰ ተጠያቂ ነው። ይህ የፍትሐብሔር ከውል ውጪ ሃላፊነት በወንጀል ህግ በአስቀጪነት የተደነገጉ ወንጀሎችን ሆን ብሎ ወይም በቸልተኛነት (የ1996 የወንጀል ህግ አንቀጽ 57 እና 59 መሰረት) ማድረግ ጋር ተመሳሳይ ነው። ነግር ግን የማስረጃ ምዘና ጎደቱ እና መጠኑ ይለያያል። ሌላው በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 2035 መሰረት አንድ ሰው በህጉ ላይ በልዩ ሁኔታ የተቀመጠውን ድንጋጌ፣ ልዩ ሁኔታ፣ደንብ እና ስርአት የጣሰ እንደሆነ ጥፋተኛ ነው ሲል ደንግጎ ይገኛል። በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት ህግን አለማወቅ ይቅርታ አያሰጥም።

2.6. ሀሰተኛ ሰነድ መፍጠር ወይም መገልገል የሚያስከትለው የፍትሐብሔር ተጠያቂነት

ሀሰተኛ ሰነድ በማዘጋጀት እና በመጠቀም ወንጀል የሚያስከትለውን የፍትሐብሔር ሀላፊነትም ስናየው እላይ ካነሳናቸው ሀሳቦች ጋር የሚጣጣም ሲሆን ወንጀለኛው ሀሰተኛ ሰነድ በማዘጋጀቱ ወይም ሌላ ሰው ባዘጋጀው ሀሰተኛ ሰነድ በመገልገሉ ከወንጀል ተጠያቂነት ባሻገር የመንግስት፣ የህዝባዊ ተቋማት ወይም ሌላ ግለሰብ የገንዘብ ጥቅም ወይም ሞራል የተጎዳ ከሆነ ለደረሰው ጉዳት ተጠያቂ ነው።

በፍትሀብሔር ህጉ አንቀጽ 2035 መሰረትም የሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀትም ሆነ መገልገሉ ግልጽ የሆነ ህግ የጣሰ ከሆነ በወንጀል አድራጊዎች ላይ ከወንጀል ቅጣት ባለፈ በድርጊቱ ምክንያት በግለሰቦች፣ድርጅቶች፣እና መንግሰት ላይ ለደረሰ ጉዳት ተጠያቂ ይሆናል። በዚሁ በሀሰተኛ ሰነድ ዝግጅት እና መጠቀም ወንጀል ምክንያት በጥፋት ላይ ተመስርቶም ይሁን ግልጽ ህግን በመተላለፍ የሚመጣ ሀላፊነት መኖሩ ከተረጋገጠ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ

2090 እና ቀጠሎ ባሉ ድንጋጌዎች መሰረት በድርጊቱ ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች ወይም ድርጅቶች ከደረሰው ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ካሳ እንዲከፍል በፍርድ ቤት ሊወሰንበት/ባት ይችላል። ስለዚህ ሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀት እና መገልገል ከወንጀል ቅጣት ባለፈ በፍትሀብሔራዊ ሀላፊነትን ሊያስከትል ይችላል።

2.7. ሀሰተኛ የሰነድ ማስረጃ የሚያስከትለው አስተዳደራዊ ሀላፊነት

የሀሰተኛ ሰነድ አዘጋጆች ወይም ተጠቃሚዎች ከወንጀል እና የፍትሐብሔር ተጠያቂነት ባለፈ በአስተዳደራዊ ተጠያቂነትም አለባቸው። አጥፊዎቹ በሚሰሩበት መስሪያ ቤት ይሄንን ድርጊት ከፈጸሙ የተፈጸመበት መስሪያቤት አጥፊዎቹን በአተዳደራዊ ውሳኔ ከቀላል የዲሲፕሊን ቅጣት እስከ ከባዱ ከስራ ማሰናበት ውሳኔ ድረስ ሊወሰን ይችላል። ይህ የአስተዳደራዊ ሀላፊነት ወንጀሉ በተፈጸመበት ተቋም አይነት ሊለያይ ይችላል።

የወንጀል ተግባር በወንጀል ግህ ማስጠየቁ እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህ በተጨማሪ የወንጀል ድርጊት በስራ ቦታ መፈጸም ከባድ የዲሲፕሊን ግድፈት እንደሆነ የሚታወቅ ሀቅ ነው። በተለይም እንደ ሀሰተኛ ሰነድ መፍጠር እና መገልገል ያሉ ወንጀሎችን በሚሰሩበት ተቋም ላይ መፈጸም በስራ ሀላፊነት በተሰጣለ እምነት ላይ የሚፈጸም ከባድ የእምነት ማጉደል ተግባር ነው። በዚሁም መሰረት ሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀቱም ሆነ መገልገል ወንጀሉ በመንግስት ተቋማት ሰነዶች ላይ የተፈጸመ እና አጥፊዎቹም የመንግስተ ሰራተኛ ከሆነ በፌደራል የመንግሰት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2002 አንቀጽ 69 እና 70 መሰረት እንደ ደረሰው ጉዳት መጠን እና አጥፊው አደገኛነት ደረጃ እና በፈጸመው የተጣለበትን እምነት ማጉደል ወንጀል ምክንያት በመንግሰት ስራው ላይ ያደረሰው ጉዳት መጠን በከባድ የዲሲፒሊን ጥፋት ከስራ እስከ ማሰናበት ድረስ ሊወሰንበት ይችላል።

በሌላ በኩል ወንጀሉ የተፈጸመው በመንግስት የልማት ድርጅት ፣ በህዝባዊ ድርጅት ወይም በግል ድርጅት ሰራተኛ ከሆነ በአሰሪ እና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27(ሰ) መሰረት ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ከሚያሰናብቱባቸው ምክንያቶች መካከል እንዲህ አይነቱን ወንጀል መፈጸም አንዱ ምክንያት ነው። በመሆኑም ሀሰተኛ ሰነድ የፈጠረው ወይም በሀሰት የተዘጋጀውን ሰነድ፤ ይሄንኑ እያወቀ የተጠቀመው አጥፊው የነዚሁ መስሪያቤቶች ሰራተኛ ከሆነ ድርጅቶቹ ግለሰቡን በወንጀል አስቀጥተው በፍትሀብሔር ሀላፊነት በፍትሐብሔር ህጉ መሰረት በድርጅቶቹ የገንዘብ ጥቅም ላይ ለደረሰው ጉዳት ተገቢውን ካሳ ከማስከፈል ባለፈ ይህ

ግለሰብ ለፈጸመው ጥፋት በዲሲፕሊን ከሰው ከስራ እስከማሰናበት የሚችሉበት የህግ መሰረት ያለ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል።

በጥቅሉ ሀሰተኛ ሰነድ መፍጠርም ሆነ መገልገል በወንጀል፣በፍትሐብሔር እንዲሁም በአስተዳደር የሚያስጠይቅ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል።

ማጠቃለያ

በዚህ የስልጠና መስጫ ጽሁፍ ስለ ሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀት እና መገልገል የህግ ተጠያቂነት ላይ ለማህበረሰቡ ይጠቅማሉ ብለን ያሰብናቸው የግንዛቤ ማስጨበጫ ሀሳቦችን ያነሳን ሲሆን በዋናነት አንባቢያን ስለ ጉዳዩ ግልጽ መረዳት እንዲኖራቸው ባማስብ አስቀድመን ስለ ሰነድ፣ የማስረጃ አይነቶች፣ ሀሰተኛ ማስረጃ፣ ሀሰተኛ የሰነድ ማስረጃዎች ምንነት ዙሪያ ጥቅል የሆኑ ሀሳቦች ተዳሰዋል።

በመቀጠልም በሁለተኛው ክፍል ከህግ ተጠያቂነት አንጻር ሀሰተኛ ሰነድ መፍጠርም ሆነ መገልገል የሚያስከትለውን ተጠያቂነት ተብራርቷል። በዚህም የፍትሐብሔር፣የወንጀል እና አስተዳደራዊ ተጠያቂነቶች ባጭሩ የተዳሰሱ ሲሆን ከሀሰተኛ ሰነዶች ማዘጋጀት እና መገልገል ወንጀል ጋር በተያዘ ወንጀል አድራጊው ላይ ስለሚኖር ተጠያቂነት በዚሁ አግባብ ለማብራራት ተሞክሯል።

ሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀትም ሆነ በሀሰት የተፈጠረን ሰነድ መገልገል የዜጎችን መሰረታዊ እና ሰብአዊ መብቶች ያለ አግባብ በመንጠቅ መብቱ ለማይገባቸው ሰዎች እንዲተላለፍ በማድረግ የሰብአዊ መብት ጥሰት እዲስፋፋ የሚያደርግ ሲሆን ከመንግስት እና ህዝብ ጥቅም አንጻርም በሀሰት በሚፈበረኩ ሰነዶች ምክንያት የህዝብ እና የሀገር ንብረት አለአግባብ እንዲመዘበር በማድረግ ለሙስና እና ሌላች የኢኮኖሚ ወንጀሎች መበራከት ዋነና መሳሪያ ሆኖ የሚያገለግል የወንጀል ተግባር ነው። በጥቅሉ ሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀት እና መግልገል ህብረተሰቡ ላይ የሚያደርሰው ጉዳት ከፍተኛ ሲሆን ከህግ ተጠያቂነት አንጻርም ፈጻሚዎቹን ወንጀሉ ወጥ በሆነ ሁኔታ የሚያስጠይቅ ነው። የፍትህብሔር እና አስተዳደራዊ ሃላፊነትን በተመለከተ የሀሰት ትግባር እንደተፈጸመበት ሰነድ ባህሪ እና ወንጀሉ እንድተፈጸመበት ድርጅት ማለትም የመንግስት፣ የመንግስት የልማት ድርጅት፣ ህዝባዊ ድርጅት ወይም የግል ድርጅት አይነት

በፍትሐብሔር ህጉ፣ በመንገስት ሰራተች አስተዳደር አዋጅ ወይም በአሰሪ እና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሰረት የሚያስጠይቅ ነው። በዚህም ጉዳት ለደረሰበት ወግን ካሳን መክፈሉ እንደተጠበቀ ሆኖ በአስተዳደራዊ የዲሰፕሊን ቅጣት ከስራ እስከመባረር የሚደርስ ከባድ ቅጣትን የሚስያከትል የወንጀል ተግባር ነው።

ማህበረሰቡ እነዚህ ወንጀለኞች ወንጀሉን የሚፈጽሙበትን ምቹ ሁኔታ እንዳይፈጠር ከፍትህ አካላት ጋር በመተባበር የወንጀል መከላከል ስራዎችንን መርዳት አለበት።። ወንጀሉ ተፈጽሞ ሲገኝ ደግሞ አስፈላጊውን ጥቆማ በመስጠት እና ምስክር በመሆን አጥፊዎች እንዲቀጡ እና ሌሎችም እንዲማሩ በማድረግ ሂደት የአንበሳውን ድርሻ የሚወጣው ህዝቡ እንደመሆኑ አስፈላጊውን ለፍትህ እርዳታ የመስጠት ሀላፊነቱን መወጣት አለበት። የፍትህ አካላት በፊናቸው ይህንኑ የማህበረሰቡን ጥረት በማስተባበር በህግ የተጣለባቸውን ሀላፊነት በመወጣት ይህን ወንጀል የፈጸሙ ሰዎች ለህግ እንዲቀርቡ እና እንዲቀጡ ማድረግ አለባቸው፣

<u>ዋቢ መጻህፍት</u>

- የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ፣1996
- የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.የወንጀል ፍትህ ፖሊሲ፣2011
- የፍትሐብሔር ህግ፣ 1952
- የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007
- የተሻሻለው ልዩ የጸረ ሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 434/1997(በአዋጅ ቁጥር 882/2007 እንደተሻሻለው)
- የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር983/2008
- የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 (በአዋጅ 1160/2011 እንደተሻሻለው)
- የሰነዶች ማረጋገጫ እና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 922/2008
- የመንግሰት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010
- የአሰሪ እና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011
- በሰው መነገድ እና ሰውን በህገወጥ መንገድ ድምበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር 1178/2012
- የወሳኝ ኩነት ምዝገባ እና ብሄራዊ መታወቂያ አዋጅ ቁጥር 760/2004

- **የአማርኛ መዝገበ ቃላት፣ የኢትየጵያ ቋንቋዎች ጥናት እና ምርምር ማእከል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣** 1993
- **አማርኛ መዝገበ ቃላት አለቃ ኪዳነወልድ ክፍሌ ፣ መጽሀፈ ሰዋስው ወግስ፣መዝገበ ቃላት**
- Blacks Law Dictionery 10th Edition



የፍትሕ ሚኒስቴር
MINISTRY OF JUSTICE

+251115-51-50-99

6044

0115-51-77-75

1370

info@eag.gov.et

የፍትሕ ሚኒስቴር
MINISTRY OF JUSTICE

አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia